**SIDAAMU DAGOOMU QOQQOWI MOOTIMMA AFFINI GAAZEEXA**

**የሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት አፍኒ ጋዜጣ**

**SIDAAMA NATIONAL REGIONAL STATE AFFINI GAZETA**

| | | |
|---|---|---|
| 5ki Diro Kiiro 45<br>Hawaasa, Ammajje 20, 2017 M.D | Sidaamu Dagoomu Qoqqowi Mootimma Amaalete Mini Allaalshi Hundaanni Fulino<br>በሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ | ፭ኛ ዓመት ቁጥር ፵፭<br>ሀዋሳ፣የካቲት ፳ ቀን ፳፻፲፯ ዓ.ም |


**Amado**

**Lallawu Kiiro 45/2017**

**Sidaamu Dagoomu Qoqqowi Mootimma Biillooyunni Ka'ino Jeefisiisaanote Bissa, Dagate Dooramaanonna Yooaanchimmate Bissa Qoossonna Horo Murate Fulino Lallawa ……….Qoola……**

**ማውጫ**

**አዋጅ ቁጥር ፵፭/፳፻፲፯**

**የሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ከኃላፊነት የተነሱ አስፈጻሚ አካላት፣ የሕዝብ ተመራጮች እና የዳኝነት አካላት መብትና ጥቅሞችን ለመወሰን የወጣ አዋጅ……………….………………..ገጽ………**


**Lallawu Kiiro 45/2017**

**Sidaamu Dagoomu Qoqqowi Mootimma Biillooyunni Ka'ino Jeefisiisaanote Bissa, Dagate Dooramaanonna Yooaanchimmate Bissa Qoossonna Horo Murate Fulino Lallawa**

**Bitima**

Mootimmanniti jeefisiisaano bissa, dagate dooramaano, xaphoomunna aliidi yoo mini pirezidantooti, xaphoomu yoo mini yooaanonna qoqqowu biiro deerrinni noo seeru allaalaano

**አዋጅ ቁጥር ፵፭/፳፻፲፯**

**የሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ከኃላፊነት የተነሱ አስፈጻሚ አካላት፣ የሕዝብ ተመራጮች እና የዳኝነት አካላት መብትና ጥቅሞችን ለመወሰን የወጣ አዋጅ**

**መግቢያ**

የመንግሥት አስፈጻሚ አካላት፣ የሕዝብ ተመራጮች፣ የጠቅላይና የከፍተኛ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንቶች፣ የጠቅላይ ፍርድ ቤት ዳኞች እና በክልሉ ቢሮ ያሉ አቃቢያነ ሕግ የተጣለባቸውን ሕዝባዊ አደራ በመወጣት

uynoonnisata dagate eeggo fulatenni qoqqowu daga horora loossannore ikkansanni biilloonyunni ka’anno yannara agarooshshenna amadooshshe assinansara hasiisannoha ikke leellinohura;

ለክልሉ ሕዝብ ጥቅም የሚሠሩ በመሆናቸው ከኃላፊነት ሲነሱ ጥበቃና እንክብካቤ እንዲደረግላቸው ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

Mootimmanniti jeefisiisaano bissa, dagate dooramaano, xaphoomunna aliidi yoo mini pirezidantooti, xaphoomu yoo mini yooaanonna qoqqowu biiro deerrinni noo seeru allaalaano biilloonyu aana keeshshitu yannara afidhino egennonna rosicho loosu aana hosiisatenni daga owaata dandiitaranna albiidinsa heeshshora yaaddukkinni dagate latishshiranna lophora ammanamatenni kaajjite loossanno gede injo kalaqa hasiissinohura;

የመንግሥት አስፈጻሚ አካላት፣ የሕዝብ ተመራጮች፣ የጠቅላይና የከፍተኛ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንቶች፣ የጠቅላይ ፍርድ ቤት ዳኞች እና በክልሉ ቢሮ ያሉ አቃቢያነ ሕግ በኃላፊነት ላይ በቆዩበት ወቅት ያካበቱትን እውቀትና ልምድ ሥራ ላይ በማዋል ሕዝቡን ማገልገል እንዲችሉና ስለ ወደ ፊት ኑሯቸው ሳያስቡ ለክልሉ ልማትና እድገት በታማኝነት ጠንክረው መሥራት የሚችሉበትን አመቺ ሁኔታዎች መፍጠር በማስፈለጉ፤

Qoqqowu Lallawi kiiro 8/2012 M.D garinni loosu aana hosanno gede fajjinoonnihu Wodiidi Daga, Dagoominna Manni Qoqqowi Biillonyunni Ka’ino Aliidi Loosu Sooreeyye, Amaalete Mini Miillanna Yooaanote Qoossonna Horo Murate fulino Lallawi kiiro 148/2004 aana worroonni qoossonna horo yannate ikoonoomete soorro ledo xaaddannokkita ikkite leeltinohura;

በክልሉ አዋጅ ቁጥር 8/2012 ዓ.ም መሠረት ሥራ ላይ እንድዉል በተፈቀደዉ የደቡብ ብሔር፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል ከኃላፊነት የተነሱ ከፍተኛ የሥራ ኃላፊዎች፣ የምክር ቤት አባላትና ዳኞች መብቶችና ጥቅሞች ለመወሰን በወጣዉ አዋጅ ቁጥር 148/2004 ላይ የተደነገጉት መብቶችና ጥቅሞች ከወቅቱ የኢኮኖሚ ለውጥና ሁኔታ ጋር የማይጣጣሙ ሆነዉ ስለተገኙ፤

Qoqqowu Bayriidi Seeri quwa 48 Cinaancho quwa 3 (a) garinni aaninoha lallamboonni.

በክልሉ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 48 ንዑስ አንቀጽ 3 (ሀ) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

## Gafa Mite

## Xaphooma

### 1. Harancho Umo

Konne Lallawa "**Sidaamu Dagoomu Qoqqowi Mootimma Biillooyunni Ka'ino Jeefisiisaanote Bissa, Dagate Dooramaanonna Yooaanchimmate Bissa Qoossonna Horo Murate Fulino Lallawa kiiro 45/2017 M.D**" yine xawisa dandiinanni.

### 2. Qaalu Tiro

Qaalu eo wole tiro uysiissannota ikka hoogguro konni Lallawi giddo:-

1. "**Qoqqowo**" yaa Sidaamu Dagoomu Qoqqowooti;
2. "**Amaalete Mine**" yaa Sidaamu Dagoomu Qoqqowi Amaale Mineeti;
3. "**Gashshootu Amaale Mine**" yaa Qoqqowu Bayriidi Seeri garinni uurrino jeefisiisaancho bisooti;
4. "**Qoqqowu Seeru Jeefisiisaano Gaamo Miila**" yaa qoqqowu pirezidanticha, 2ki pirezidanticha, Biirote sooreeyye, biirote 2ki sooreeyye, Borrote mini sooreeyye, komishiineroota, Biilloonyu, Ejensetenna wole hattoo uurrinsha sooreeyye hattono rejiopolitanete quchumi Kantiiwanna 2ki Kantiiwa, Zoonete Qara Gashshaancho, Zoonete 2ki Gashshaanchonna konni deerrinni mootoonsinoonnire amaddanno;

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

### 1. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "**የሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ከኃላፊነት የተነሱ አስፈጻሚ አካላት፣ የሕዝብ ተመራጮች እና የዳኝነት አካላት መብትና ጥቅሞችን ለመወሰን የወጣ አዋጅ ቁጥር ፵፭/፳፻፲፯ ዓ.ም**" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### 2. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፡-

1. "**ክልል**" ማለት የሲዳማ ብሔራዊ ክልል ነው፤
2. "**ምክር ቤት**" ማለት የሲዳማ ብሔራዊ ክልል ምክር ቤት ነው፤
3. "**መስተዳድር ምክር ቤት**" ማለት በክልሉ ሕገ-መንግሥት መሠረት የተቋቋመ አስፈጻሚ አካል ነው፤
4. "**የክልሉ ሕግ አስፈፃሚ ምድብ አባል**" ማለት ርዕሰ መስተዳድሩን፣ ምክትል ርዕሰ መስተዳድሩን፣ የቢሮ ኃላፊዎችን፣ ምክትል የቢሮ ኃላፊዎችን፣ የዞን አስተዳዳሪዎችን፣ ምክትል አስተዳዳሪዎችን፣ የጽህፈት ቤት ኃላፊዎችን፣ ኮሚሽነሮችን፣ የባለስልጣን፣ የኤጀንሲ እና የሌላ ማናቸውም ተመሳሳይ ተቋም ኃላፊዎችን፣ ምክትል ኃላፊዎችን እንዲሁም የሬጂኦፖሊታን ከተማ ከንቲባ እና ምክትል ከንቲባን፣ የዞን አስተዳዳሪን፣ ምክትል አስተዳዳሪን እና በዚሁ ደረጃ የተሾሙትን ያጠቃልላል፤

5. **"Qoqqowu Seera Fushshitanno Gaamo Miila"** yaa Qoqqowu Songaaficha, $2^{ki}$ Songaaficha, Amaalete mini miilla, Uurrinshu komite ganbisaano, $2^{ki}$ ganbisaano, borrote mini sooreessa, rejiopolitanete quchumi Songaafichanna $2^{ki}$ Songaaficha amaddanno;

6. **"Qoqqowu Seera Tirtanno Gaamo Miila"** yaa Xaphoomu yoo mini pirezidanticha, $2^{ki}$ pirezidanticha, Xaphoomu Yoo Mini Yooaano, Zoonete Aliidi yoo mini pirezidantichanna $2^{ki}$ pirezidanticha, rejiopolitanete quchumi Aliidi Yoo Mini pirezidantichanna $2^{ki}$ pirezidanticha hanqaffanno;

7. **"Qoqqowu Pirezidantichi Cinaancho Gaamo"** yaa Qoqqowu Pirezidanticha, $2^{ki}$ Pirezidantichanna konni deerrinni mootoonsinoonnire hanqaffanno;

8. **"Biirote Sooreeyye Cinaancho Gaamo"** yaa Biirote Sooreeyye, Biirote sooreeyye deerrinni mootoonsinoonnire, Zoonete qara gashshaancho woy konni deerrinni mootoonsinoonnirenna rejiopolitanete quchumi kantiiwa hanqaffanno;

9. **“Komishiinerootunna Dayrekiterootu Cinaancho Gaamo”** yaa Komishiinete Komishiinere, Biilloonyu Qara Dayrekitere, Ejensete Qara Dayrekiterenna Inistitiyuutete Qara Dayrekitere hanqaffanno;

5. **“የክልሉ ሕግ አውጭ ምድብ አባል”** ማለት የክልሉን ምክር ቤት አፈ-ጉባኤን፣ ምክትል አፈ-ጉባኤን፣ የምክር ቤት አባላትን፣ የምክር ቤት ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢዎችን፣ ምክትል ሰብሳቢዎችን፣ የጽህፈት ቤት ኃላፊን፣ የሬጂኦፖሊታን ከተማ ምክር ቤት አፈ ጉባኤንና ምክትል አፈ ጉባኤን ይጨምራል፤

6. **“የክልሉ ሕግ ተርጓሚ ምድብ አባል”** ማለት የክልሉን ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት፣ ምክትል ፕሬዚዳንት፣ የጠቅላይ ፍርድ ቤት ዳኞች፣ የዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንትና ምክትል ፕሬዚደንት፣ የሬጂኦፖሊታን ከተማ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት እና ምክትል ፕሬዚዳንትን ያጠቃልላል፤

7. **“የክልሉ ርዕሰ መስተዳድር ንዑስ ምድብ”** ማለት ርዕሰ መስተዳድሩን፣ ምክትል ርዕሰ መስተዳደሩንና በተመሳሳይ ደረጃ ያሉትን ያጠቃልላል፤

8. **“የቢሮ ኃላፊዎች ንዑስ ምድብ”** ማለት የቢሮ ኃላፊዎችን፣ በቢሮ ኃላፊ ደረጃ ተሿሚዎችን፣ የዞን አስተዳዳሪዎችን ወይም በተመሳሳይ ደረጃ የሚገኙ የሥራ ኃላፊዎችንና የሬጂኦፖሊታን ከተማ ከንቲባን የሚያጠቃልል ነው፤

9. **“ኮሚሽነሮችና ዳይሬክተሮች ንዑስ ምድብ“** ማለት የኮሚሽን ኮሚሽነር፣ የባለሥልጣን ዋና ዳይሬክተር፣ የኤጀንሲ ዋና ዳሬክተር እና የኢንስቲትዩት ዋና ዳይሬክቴርን የሚያጠቃልል ነዉ፤

10. **"Layinki Biirote Sooreeyye Cinaancho Gaamo"** yaa $2^{ki}$ Biirote sooreessa, zoonete $2^{ki}$ Gashshaancho, rijiopolitanete quchumi $2^{ki}$ kantiiwa woy konni deerrinni mootoonsinoonnire hanqaffanno;

11. **"Xaphoomu Yoo Mini Pirezidantichi Cinaancho Gaamo"** yaa Xaphoomu yoo mini pirezidantichanna $2^{ki}$ pirezidanticha hanqaffanno;

12. **"Seeru Allaalshi Cinaancho Gaamo"** yaa Qoqqowu Farcote Biiro deerrinni heedhanno seeru allaalaanooti;

13. **"Xaphoomu Yoo Mini Yooaano Cinaancho Gaamo"** yaa Xaphoomu Yoo Mini Yooaanoo, Aliidi Yoo Mini pirezidantichanna Layinki pirezidantichaati;

14. **"Mootimmate Uurrinsha"** yaa tirfete uurrinokki mootimma bajeette gaantanno mootimmate loosu mineeti;

15. **"Daaragoote"** yaa konni Lallawira worroonni qoossonna horo af'rate qoosso noonsari aliidi loosu sooreeyyera xeinsoonnikki damoozu baatooshsheeti;

16. **"Umo Dandaate Baatooshshe"** yaa ayno aliidi loosu sooreessi mootimmate loosi biilloonyinni owaatanni keeshshe mootimmate loosi biillooyninni kairo umosi dandaate daaragootete daninni uynannisi baatooshsheeti;

10. **"የምክትል ቢሮ ኃላፊዎች ንውስ ምድብ"** ማለት ምክትል ቢሮ ኃላፊ፣ የዞን ምክትል አስተዳዳሪዎችን፣ የሪጂዮፖሊታን ከተማ ምክትል ከንቲባዎችን ወይም በተመሳሳይ ደረጃ የተሾሙትን ያጠቃልላል፤

11. **"የጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዝዳንት ንውስ ምድብ"** ማለት የክልሉን ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዝዳንትንና ምክትል ፕሬዝዳንትን ያጠቃልላል፤

12. **"የዐቃቤያነ ሕግ ንውስ ምድብ"** ማለት በክልል ፍትህ ቢሮ በቢሮ ደረጃ ያሉ ዐቃቤያነ ሕግ ማለት ነው፤

13. **"የጠቅላይ ፍርድ ቤት ዳኞች ንውስ ምድብ"** ማለት የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ዳኞች፣ የከፍተኛ ፍርድ ቤት ፕሬዝዳንትና ምክትል ፕሬዝዳንት ማለት ነዉ፤

14. **"የመንግሥት ተቋም"** ማለት ለትርፍ ያልተቋቋመ በመንግሥት በጀት የሚመደብለት የመንግሥት መሥሪያ ቤት ነው፤

15. **"ዳረጎት"** ማለት በዚህ አዋጅ የተደነገጉ መብትና ጥቅሞችን የማግኘት መብት ያላቸው ከፍተኛ የሥራ ኃላፊዎች ያልተጣራ ደመወዛቸው ክፍያ ነው፤

16. **"የመቋቋሚያ አበል"** ማለት ማንኛውም ከፍተኛ የሥራ ኃላፊ በመንግሥት የሥራ ኃላፊነት ሲያገለግል ቆይቶ ከመንግሥት የሥራ ኃላፊነት ሲነሣ እራሱን እንዲያቋቁም በዳረጎት መልክ የሚሰጠው ክፍያ ነው፤

17. **"Biilloonyunni Geegiissa"** yaa ayno mootimmate aliidi biilloonyinni owaatanni noo loosu sooreessi sooreessimmatenni geegiissate;

18. **"Biilloonyunni Geegiissate Baatooshshe"** yaa mootimmate aliidi biilloonyinni qoqqowo owaatanni noohu loosu sooreessi yawosinni geegissamanno yannara uyno owaantera daaragootete daninni xeinsikki baantanni damoozu baatooshsheeti;

19. **"Biilloonyunni Kainoho"** yaa hajo la'annosi bisinni fajjinikkinni biilloonyesi agurannoha woy jaddo looseenna hunaanchimma yoote mine buunxoonniha agurranna wolu korkaatinni qoqqowu mootimma gumulonni biilloonyunni ka"anno gede assinoonniha, xissotenni woy bisu gawajjonni woy wolqate ale ikkino korkaatinni biilloonyunni kaino konni Lallawi garinni qoosso noosi manchooti;

20. **''Qoosso Noosihu"** yaa konni Lallawi garinni uynanni qoossonna horo afi'rate ikkado ikkinohu woy afi'rate aana noohu qoqqowu mootimma seeru jeefisiisaanchi, seeru fushshaanchinna seeru tiraanchi gaamo miilaati;

21. **"Maatete"** yaa ayeno qoosso noosihura galtenna dirinsa iillinokki ooso amadanno;

22. **"Riqiwaancho"** yaa garimma noosi wommete seerinni uynoonni tiro amadanno**;**

17. **"ከኃላፊነት ስንብት"** ማለት ማንኛውም በመንግሥት ከፍተኛ ኃላፊነት ላይ ሲያገለግል የነበረ የሥራ ኃላፊ ከኃላፊነት መሰናበት ነዉ፤

18. **"የኃላፊነት ስንብት ክፍያ"** ማለት በመንግሥት ከፍተኛ ኃላፊነት ክልሉን ሲያገለግል የነበረ የሥራ ኃላፊ ከኃላፊነት በሚሰናበትበት ጊዜ ላበረከተው አስተዋጽኦ በዳረጎት መልክ የሚከፈለው ያልተጣራ ደመወዝ ክፍያ ነው፤

19. **"ከኃላፊነት የተነሣ"** ማለት በሚመለከተው አካል ሳይፈቀድለት ኃላፊነቱን የሚለቅቀዉን ወይም ወንጀል ፈጽሞ ጥፋተኝነቱ በፍርድ ቤት ከተረጋገጠዉ በስተቀር በሌላ ምክንያት በክልሉ መንግሥት ውሣኔ ከሥልጣኑ እንዲነሣ የተደረገ፣ በሕመም ወይም በአካል ጉዳት ወይም ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ከኃላፊነቱ የተነሣ በዚህ አዋጅ መሠረት ባለመብት የሆነ ሰዉ ነው፤

20. **"ባለመብት"** ማለት በዚህ አዋጅ መሠረት የሚሰጡ መብቶችና ጥቅሞችን ለማግኘት ብቁ የሆነ ወይም በማግኘት ላይ ያለ የክልሉ መንግሥት ሕግ አስፈፃሚ፣ ሕግ አውጪ እና ሕግ ተርጓሚ ምድብ አባል ነው፤

21. **"ቤተሰብ"** ማለት የማንኛውም ባለመብት የትዳር ጓደኛና አካለ መጠን ያልደረሱ ልጆችን ያጠቃልላል፤

22. **"ተተኪ"** ማለት አግባብ ባለው የጡረታ ሕግ

23. "**Doorshu Diro**" yaa gobbanke doorshi Lallawi garinni ontu diri owaante yannaati.

**3. Kooteemmate Xawishsha**

Konni Lallawi giddo mitte kooteemmanni xawinsoonnihu wole kooteemmano amadannoho.

4. **Jeefishshu Mamigeeshsha**

Kuni Lallawi biilloonyu aana keeshshite biilloonyunni ka’ino mootimmate jeefisiisaano bissa, dagate dooramaano, xaphoomu yoo mini pirezidantooti, layinki pirezidantooti, xaphoomu yoo mini yooaano, aliidi yoo mini pirezidantooti, layinki pirezidantootinna biirote deerrinni heedhanno seeru allaalaano aana jeefamannoha ikkanno.

**Gafa 2**

**Biilloonyunni Ka’ino Mootimmate Jeefisiisaano Gaamo Miilla Qoossonna Horo**

**5. Wommete Qoosso**

1. Wommete seerinni seerroonniri noo gedeenni hee’reenna ajay ajeenna mitto wo’ma doorshu dironna hakkuy aleenni owaantohu ayno qoqqowu seera jeefisiissano gaamo miili;-

a) Biilloonyunni ka’’ano yannara dirisi 50 nna ale ikkiro wommete owaante baatooshshe heeshshosi diri geeshsha baantannisi;

b) Xissote korkaatinni biilloonyunni kairo xissote womme baatooshshe heeshshosi

የተሰጠውን ትርጓሜ ይይዛል፤

23. “**የምርጫ ዘመን**” ማለት በሀገራችን ምርጫ አዋጅ መሠረት አምስት ዓመት የአገልግሎት ጊዜ ነው፡፡

**3. የጾታ አገላለጽ**

በዚህ አዋጅ ውስጥ በአንድ ጾታ የተገለጸው ሌላኛዉንም ጾታ ያካትታል፡፡

**4. የተፈጻሚነት ወሰን**

ይህ አዋጅ በኃላፊነት ላይ ቆይተው ከኃላፊነት በሚነሱ የመንግሥት አስፈጻሚ አካላት፣ የሕዝብ ተመራጮች፣ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕረዝዳንቶች፣ ምክትል ፕረዝዳንቶች፣ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ዳኞች፣ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ፕረዝዳንቶች፣ ምክትል ፕረዝዳንቶች እና በቢሮ ደረጃ የሚገኙ አቃቤ ሕጎች ላይ ተፈጻሚነት ይኖረዋል፡፡

**ክፍል ሁለት**

**ከኃላፊነት የተነሡ የሕግ አስፈፃሚ ምድብ አባላት መብቶችና ጥቅሞች**

**5. የጡረታ መብት**

1. በጡረታ ሕግ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ቢያንስ አንድ ሙሉ የምርጫ ዘመን እና ከዚያ በላይ ያገለገለ ማንኛውም የክልሉ ሕግ አስፈጻሚ ምድብ አባል፡-

ሀ) ከኃላፊነት በሚነሳበት ወቅት ዕድሜው 50 (ሃምሳ) ዓመትና ከዚያ በላይ ከሆነ የአገልግሎት ጡረታ አበል እስከ ዕድሜ ልክ ይከፈለዋል፤

ለ) በህመም ምክንያት ከኃላፊነት ከተነሳ የህመም

diri geeshsha baantannisi;

c) Loosu aana hee’re tenne kalqenni reyoote baxxiro ragi’raanote wommete baatooshshe baantanni.

2. Konni quwira cinaancho quwa (1) hunda tittirroonnihu ayee mootimmate biilloonyira mittu doorshu diri woroonni owaantohu:-

a) Biillonyunni ka’’anno yannara dirisi 50 (ontaawo) wo’minoha ikkiro owantete daaragoote baantannisi;

b) Xissote korkaatinni biilloonyunni kairo xissote daaragoote baantannisi;

3. Konni quwira cinaanchu quwa (1) nna (2) hunda seerroonni baatooshshuwa wommete seeri garinni jeefinsanniha ikkanno.

**6. Umo Dandaate Baatooshshe**

1. Biilloonyunni Ka’ino Mootimmate Jeefisiisaano Gaamo Miillara Umo Dandaate Baatooshshe uynannihu aane noo garinni ikkanno:-

a) Ajay ajeenna mittu doorshu diri owaante ee billoonyunni kairo; woy

b) Bocu doorshu diro ajjinokki owaante ee xissotenni, bisu gawajjonni woy wolqate aleenni ikkino wolu korkaatinni billoonyunni kairo umo dandaate baatooshshe baantannisi.

2. Konni quwira cinaancho quwa (1) hundaanni xawinsoonnihu mootimmate biiltora umo dandaate baatooshshe baantannihu umi mittu doorshu diri owaantera lamalu (7) agani

ጡረታ አበል እስከ ዕድሜ ልክ ይከፈለዋል፤

ሐ) በሥራ ላይ እያለ ከዚህ ዓለም በሞት ቢለይ ለተተኪዎቹ የጡረታ አበል ይከፈላል፤

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ሥር የተዘረዘረው ማንኛውም የመንግሥት ተሿሚ ከአንድ ምርጫ ዘመን በታች አገልግሎ፡-

ሀ) ከኃላፊነት ሲነሳ ዕድሜው 50 (ሃምሳ) ዓመት የሞላው ከሆነ የአገልግሎት ዳረጎት ይከፈለዋል፤

ለ) በህመም ምክንያት ከኃላፊነት ከተነሳ የህመም ዳረጎት ይከፈለዋል፤

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እና (2) ሥር የተደነገጉት ክፍያዎች በጡረታ ሕግ መሠረት የሚፈጸሙ ይሆናል፡፡

**6. የመቋቋሚያ አበል**

1. ከኃላፊነት ለተነሡ የሕግ አስፈፃሚ ምድብ አባላት የመቋቋሚያ አበል የሚከፈለዉ እንደሚከተለዉ ይሆናል፡-

ሀ) ቢያንስ አንድ የምርጫ ዘመን አገልግሎ ከኃላፊነት ከተነሳ፤ ወይም

ለ) ከግማሽ ያላነሰ የምርጫ ዘመን አገልግሎ በህመም፣ በአካል ጉዳት ወይም ከአቅም በላይ በሆነ ሌላ ምክንያት ከኃላፊነት ከተነሳ የመቋቋሚያ አበል ይከፈለዋል፤

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ሥር የተዘረዘረው ማንኛውም የመንግሥት ተሿሚ የሚከፈለው የመቋቋሚያ አበል ለመጀመሪያው የአንድ የምርጫ

damooza ikkeenna mittu doorshu diri aleenni noo mittu mittunku lexxote mittu diri owaantera goofimarchunniha mittu (1) agani damooza lende shallanganniha ikkanna lamu doorshu diri alee noo mittu mittunku lexxote diri owaantera lamu (2) agani damooza lendanni baantanni.

3. Konni quwi cinaancho quwa (2) hunda seerroonnihu hee’rirono mittu manchira baantanni xaphoomu umo dandaate baatooshshi lemiina shoolu (24) agani damooza roora dinosi.

**7. Biilloonyunni Ka”ate Baatooshshe**

1. Biilloonyunni Ka’ino Mootimmate Jeefisiisaano Gaamo Miillara biilloonyunni ka”ate baatooshshe uynanninsa.

2. Konni quwira cinaancho quwa 1 garinni biilloonyunni ka”ate baatooshshe baantannihu umi mittu doorshu diri owaantera lamalu (7) agani xeinsonnikki damooza ikkeenna mittu doorshu diri aleenni noo mittu mittunku lexxote mittu diri owaantera goofimarchunniha mittu (1) agani xeinsoonnikki damooza lende shallanganniha ikkanna lamu doorshu diri ale noo mittu mittunku lexxote diri owaantera lamu (2) agani xeinsoonnikki damooza lendanni baantanni.

ዘመን አገልግሎት የሰባት (7) ወራት ደመወዝ ሆኖ ከአምስት ዓመት በላይ ላለው ለእያንዳንዱ ተጨማሪ አንድ ዓመት አገልግሎት የመጨረሻው የአንድ (1) ወር ደመወዝ እየታከለ የሚሰላ ሲሆን ከሁለት ምርጫ ዘመን በላይ ላለው ለእያንዳንዱ ተጨማሪ አንድ ዓመት አገልግሎት የሁለት ወር (2) ወር ደመወዝ እየተጨመረ ይከፈላል፤

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) ሥር የተደነገገው ቢኖርም ለአንድ ሰው የሚከፈለው ጠቅላላ የመቋቋሚያ አበል ክፍያ ከሃያ አራት (24) ወራት ደመወዝ መብለጥ የለበትም፡፡

**7. የኃላፊነት ስንብት ክፍያ**

1. ከኃላፊነት ለተነሡ የሕግ አስፈፃሚ ምድብ አባላት የኃላፊነት ስንብት ክፍያ ይከፈላቸዋል፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት የኃላፊነት ስንብት ክፍያ የሚከፈለው ለመጀመሪያው የአንድ ምርጫ ዘመን አገልግሎት የሰባት (7) ወራት ያልተጣራ ደመወዝ ክፍያ ሆኖ ከአንድ ምርጫ ዘመን በላይ ላለው ለእያንዳንዱ ተጨማሪ የአንድ ዓመት አገልግሎት የመጨረሻው የአንድ ወር (1) ያልተጣራ ደመወዝ ክፍያ እየታከለ የሚሰላ ሲሆን ከሁለት ምርጫ ዘመን በላይ ላለው ለእያንዳንዱ ተጨማሪ የአንድ ዓመት አገልግሎት የሁለት ወር (2) ወር ያልተጣራ ደመወዝ ክፍያ እየተጨመረ ይከፈላል፡፡

3. Konni quwi cinaancho quwa 2 hunda seerroonniri hee'rirono xaphooma biilloonyunni ka''ate baatooshshi Limiina Shoole (24) agani damooza roora dinosi.

8. **Gallanni Mini Baatooshshenna Gallanni Mine**

1. Biilloonyunni Ka'ino Mootimmate Jeefisiisaano Gaamo Miillara minu kiri baatooshshenna mine uynannihu aane noo garinni ikkanno:-

a) Ajay ajeenna 1 doorshu diro owaate biilloonyunni kairo; woy

b) Boco doorshu diro ajjinokki owaante ee xissotenni, bissu gawajjonni woy wolqate aleenni ikkino wolu korkaatinni biilloonyunni kairo gallanni mini baatooshshe baantannisi.

2. Konni quwi cinaancho quwa 1 hunda seerroonni garinni gallanni mini baatooshshe mitte hinge baantaniha ikke:-

a) Qoqqowu Pirezidantichi, $2^{ki}$ prezidantichi woy konni deerrira mootoo'mitinore ikkituro kaimu baatooshshi tonnu (10) agani xeinsonnikki damoozi baatooshshe ikke mittu doorshu diri ale noo mittu-mittunku ledote diri owaantera mittu (1) agani xeinsoonnikki damoozi baatooshshe lendanniha ikke lamu doorshu diri aleenni

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 ሥር የተደነገገው ቢኖርም የሚከፈለው ጠቅላላ የኃላፊነት ስንብት ክፍያ ከሃያ አራት (24) ወራት ደመወዝ መብለጥ የለበትም፡፡

8. **የመኖሪያ ቤት አበልና መኖሪያ ቤት**

1. ከኃላፊነት ለተነሡ የሕግ አስፈፃሚ ምድብ አባላት የመኖሪያ ቤት አበልና መኖሪያ ቤት የሚሰጠዉ እንደሚከተለዉ ይሆናል፡-

ሀ) ቢያንስ አንድ የምርጫ ዘመን አገልግሎ ከኃላፊነት ከተነሳ፤ ወይም

ለ) ከግማሽ የምርጫ ዘመን ያላነሰ አገልግሎ በህመም፣ በአካል ጉዳት ወይም ከአቅም በላይ በሆነ ሌላ ምክንያት ከኃላፊነት ከተነሳ የመኖሪያ ቤት አበል ይከፈለዋል፤

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ሥር በተደነገገው መሠረት የመኖሪያ ቤት አበል በአንድ ጊዜ የሚከፈል ሆኖ፡-

ሀ) ፕሬዚዳንት፣ ምክትል ፕሬዚዳንት ወይም በተመሳሳይ ደረጃ ላይ የሚገኙ የመንግሥት ተሿሚዎች ከሆኑ የመነሻ ክፍያ የአስር (10) ወራት ያልተጣራ ደመወዝ ክፍያ ሆኖ ከአንድ የምርጫ ዘመን በላይ ላለው ለእያንዳንዱ ተጨማሪ የአንድ ዓመት አገልግሎት የአንድ (1) ወር ያልተጣራ ደመወዝ ክፍያ እየታከለ የሚሰላ ሲሆን ከሁለት የምርጫ ዘመን በላይ ላለው ለእያንዳንዱ አንድ ዓመት ተጨማሪ

noo mittu mittunku diri ledote owantera lamu (2) agani xeinsoonnikki damoozi baatooshshe lendanni baantanni.

b) Biirote sooreessi, zoonete qaru gashshaanchi rejiopolitanete quchumi kantiiwi woy konni deerrinni mootoonsinoonniha ikkiro kaimu baatooshshi lamalu agani xeinsoonnikki damooza ikkeenna mittu doorshu diri aleenni noo mittu mittunku lexxote diri owaantera mittu (1) agani xeinsonnikki damooza lende shallanganniha ikkanna lamu doorshu diri ale noo mittu mittunku lexxote diri owaantera lamu (2) agani xeinsonnikki damooza lendanni baantanni.

c) Komishiinete Komishiinere, Biilloonyu Qara Dayrekitere, Ejensete Qara Dayrekitere, Inistitiyuutete Qara Dayrekitere woy konni deerrinni mootoo'mitinori kaimu baatooshshe ontu (5) agani xeinsonnikki damooza ikkeenna mittu doorshu diri aleenni noo mittu mittunku lexxote diri owaantera mittu (1) agani xeinsoonnikki damooza lende shallanganniha ikkanna lamu doorshu diri alee noo mittu mittunku lexxote diri owaantera lamu (2) agani xeinsoonnikki damooza lendanni baantanni.

d) 2[ki] biirote sooreessinna konni deerrira mootoo'mitinori, rejiopolitanete quchumi 2[ki] kantiiwi woy konni deerrinni mootoo'mitinori kaimu baatooshshe shoolu (4) agani xeinsonnikki damooza ikkeenna mittu doorshu diri aleenni noo

አገልግሎት የሁለት ወር (2) ወር ያልተጣራ ደመወዝ ክፍያ እየተጨመረ ይከፈላል፤

ለ) የቢሮ ኃላፊ፣ የዞን ዋና አስተዳዳሪ፣ የሬጂኦፖሊታን ከተማ ከንቲባ ወይም በተመሳሳይ ደረጃ ላይ የሚገኝ የመንግሥት ተሿሚ ከሆነ የመነሻ ክፍያው ሰባት (7) ወራት ያልተጣራ ደመወዝ ክፍያ ሆኖ ከአንድ የምርጫ ዘመን በላይ ላለው ለእያንዳንዱ ተጨማሪ የአንድ ዓመት አገልግሎት የአንድ (1) ወር ያልተጣራ ደመወዝ ክፍያ እየታከለ የሚሰላ ሲሆን ከሁለት የምርጫ ዘመን በላይ ላለው ለእያንዳንዱ ተጨማሪ አንድ ዓመት አገልግሎት የሁለት ወር (2) ወር ያልተጣራ ደመወዝ እየተጨመረ ይከፈላል፤

ሐ) የኮሚሽን ኮሚሽነር፣ የባለሥልጣን ዋና ዳይሬክተር፣ የኤጀንሲ ዋና ዳሬክተር፣ የኢንስቲትዩት ዋና ዳይሬክተር ወይም በተመሳሳይ ደረጃ ላይ የሚገኙ የመንግሥት ተሿሚዎች ከሆኑ መነሻ ክፍያው የአምስት (5) ወራት ያልተጣራ ደመወዝ ሆኖ ከአንድ የምርጫ ዘመን በላይ ላለው ለእያንዳንዱ ተጨማሪ አንድ ዓመት አገልግሎት አንድ (1) ወር ደመወዝ ክፍያ እየታከለ የሚሰላ ሲሆን ከሁለት የምርጫ ዘመን በላይ ላለው ለእያንዳንዱ ተጨማሪ አገልግሎት የሁለት ወር (2) ወር ደመወዝ እየተጨመረ ይከፈላል፤

መ) ምክትል የቢሮ ኃላፊ ወይም በተመሳሳይ ደረጃ ላይ የሚገኙ የመንግሥት ተሿሚዎች፤ ለሬጂኦፖሊታን ከተማ ምክትል ከንቲባ ወይም በተመሳሳይ ደረጃ ላይ የሚገኙ የመንግሥት ተሿሚዎች ከሆኑ መነሻ ክፍያው የአራት (4) ወራት ያልተጣራ ደመወዝ ሆኖ ከአንድ የምርጫ

mittu mittunku lexxote diri owaantera mittu (1) agani xeinsoonnikki damooza lende shallanganniha ikkanna lamu doorshu diri ale noo mittu mittunku lexxote diri owaantera lamu (2) agani xeinsoonnikki damooza lendanni baantanni.

3. Konni quwira cinaancho quwa (2) fidalete diri (a-c) hunda seerroonnihu noo gedeenni hee’rirono gallanni minira bantanni baatooshshi xaphoomu Lemiinna Shoolu (24) agani damooza roora dinosi.

**9. Kaameelu Baatooshshe**

1. Biilloonyunni Ka’ino Mootimmate Jeefisiisaano Gaamo Miillara baantannihu kaameelu baatooshshi aane noo garinni ikkanno:-

a) Ajay ajeenna 1 doorshu diro owaate biilloonyunni kairo; woy

b) Boco doorshu diro ajjinokki owaante ee xissotenni, bissu gawajjonni woy wolqate aleenni ikkino wolu korkaatinni biilloonyunni kairo kameelu baatooshshe baantannisi.

2. Konni quwira cinaancho quwa (1) hunda seerroonni garinni kaameelu baatooshshi mitte hinge baantannita ikke:-

a) Qoqqowu prezidantichi, 2ki prezidantichi woy konni deerrinni mootoo’mitinorira kaimu baatooshshi lamalu (7) agani xeinsoonnikki damoozi baatooshshe ikke mittu doorshu diri ale noo mittu-mittunku

ዘመን በላይ ላለው ለእያንዳንዱ ተጨማሪ አንድ ዓመት አገልግሎት አንድ (1) ወር ደመወዝ ክፍያ እየታከለ የሚሰላ ሲሆን ከሁለት የምርጫ ዘመን በላይ ላለው ለእያንዳንዱ ተጨማሪ አገልግሎት የሁለት ወር (2) ወር ደመወዝ እየተጨመረ ይከፈላል፤

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 ከፊደል ተራ (ሀ-ሐ) ሥር የተደነገገው ቢኖርም ለመኖሪያ ቤት አበል የሚከፈለው አበል ጠቅላላ ክፍያ ከሃያ አራት (24) ወራት ደመወዝ መብለጥ የለበትም፡፡

**9. የተሽከርካሪ አበል**

1. ከኃላፊነት ለተነሡ የሕግ አስፈፃሚ ምድብ አባላት የሚከፈለዉ የተሽከርካሪ አበል እንደሚከተለዉ ይሆናል፡-

ሀ) ቢያንስ አንድ የምርጫ ዘመን አገልግሎ ከኃላፊነት ከተነሳ፤ ወይም

ለ) ከ ግማሽ ያላነሰ የምርጫ ዘመን አገልግሎ በህመም፣ በአካል ጉዳት ወይም ከአቅም በላይ በሆነ ሌላ ምክንያት ከኃላፊነት ከተነሳ የተሽከርካሪ አበል ይከፈለዋል፤

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ሥር በተደነገገው መሠረት የተሽከርካሪ አበል በአንድ ጊዜ የሚከፈል ሆኖ፡-

ሀ) የክልሉ ፕሬዚዳንት፣ ምክትል ፕሬዚዳንት ወይም በተመሳሳይ ደረጃ ላይ የሚገኝ የመንግሥት ተሿሚ ከሆነ፤ የመነሻ ክፍያው የሰባት (7) ወራት ሙሉ ደመወዝ ሆኖ ከአንድ የምርጫ ዘመን በላይ ላለው ለእያንዳንዱ ተጨማሪ

lexxote diri owaantera mittu (1) agani xeinsoonnikki damoozi baatooshshe lendenniha ikke lamu doorshu diri aleenni noo mittu mittunku ledote diri owaantera lamu (2) agani xeinsoonnikki damooza lendani baantanni.

b) Biirote sooreessi woy konni deerrinni mootoo'mitinonorira kaimu baatooshshi ontu (5) agani xeinsoonnikki damooza ikke mittu doorshu diri ale noo mittu mittunku ledote diri owaantera mittu (1) agani xeinsoonnikki damooza lende shallanganniha ikkeenna mittu doorshu diri alee noo mittu mittunku lexxote diri owaaantera lamu (2) agani xeinsoonnikki damooza lendanni baantanni.

c) Komishiinete Komishiinere, Biilloonyu Qara Dayrekitere, Ejensete Qara Dayrekitere, Inistitiyuutete Qara Dayrekitere woy konni deerrinni mootoo'mitinori kaimu baatooshshe shoolu (4) agani xeinsonnikki damooza ikkeenna mittu doorshu diri aleenni noo mittu mittunku lexxote diri owaantera mittu (1) agani xeinsoonnikki damooza lende shallanganniha ikkanna lamu doorshu diri alee noo mittu mittunku lexxote diri owaantera lamu (2) agani xeinsoonnikki damooza lendanni baantanni

d) 2ki biirote sooreessi woy konni deerrira mootoo'mitinori rejiopolitanete quchumi

የአንድ ዓመት አገልግሎት የአንድ (1) ወር ያልጣራ ደመወዝ እየታከለ የሚሰላ ሲሆን ከሁለት የምርጫ ዘመን በላይ ላለው ለእያንዳንዱ ተጨማሪ የአንድ ዓመት አገልግሎት የሁለት ወር (2) ወር ደመወዝ እየተጨመረ ይከፈላል፤

ለ) የቢሮ ኃላፊ ወይም በተመሳሳይ ደረጃ ላይ ለሚገኙ የመንግሥት ተሿሚዎች የመነሻ ክፍያው የአምስት (5) ወራት ሙሉ ደመወዝ ሆኖ ከአንድ የምርጫ ዘመን በላይ ላለው ለእያንዳንዱ ተጨማሪ የአንድ ዓመት አገልግሎት የአንድ (1) ወር ያልተጣራ ደመወዝ ክፍያ እየታከለ የሚሰላ ሲሆን ከሁለት የምርጫ ዘመን በላይ ላለው ለእያንዳንዱ ተጨማሪ አንድ ዓመት አገልግሎት የሁለት ወር (2) ወር ያልተጣራ ደመወዝ እየተጨመረ ይከፈላል፤

ሐ) የኮሚሽን ኮሚሽነር፣ የባለሥልጣን ዋና ዳይሬክተር፣ የኤጀንሲ ዋና ዳይሬክተር፣ የኢንስቲትዩት ዋና ዳይሬክተር ወይም በተመሳሳይ ደረጃ ላይ የሚገኙ የመንግሥት ተሿሚዎች ከሆኑ መነሻ ክፍያው የአራት (4) ወራት ያልተጣራ ደመወዝ ሆኖ ከአንድ የምርጫ ዘመን በላይ ላለው ለእያንዳንዱ ተጨማሪ አንድ ዓመት አገልግሎት አንድ (1) ወር ደመወዝ ክፍያ እየታከለ የሚሰላ ሲሆን ከሁለት የምርጫ ዘመን በላይ ላለው ለእያንዳንዱ ተጨማሪ አገልግሎት የሁለት ወር (2) ወር ደመወዝ እየተጨመረ ይከፈላል፤

መ) ምክትል የቢሮ ኃላፊ ወይም በተመሳሳይ ደረጃ

2ki kantiiwinna konni deerrinni mootoonsinoonniri kaimu baatooshshi sasu (3) agani xeinsoonnikki damooza ikke mittu doorshu diri ale noo mittu-mittunku ledote diri owaantera mittu (1) agani xeinsoonnikki damoozi lende shallanganniha ikkeenna lamu doorshu diri aleenni noo mittu mittunku lexxote diri owantera lamu (2) agani xeinsoonnikki damooza lendanni baantanni.

3. Konni quwira cinaancho quwa (2) fidale (a-d) hunda seerroonnihu he’rirono kaameelu baatooshshira baantannihu xaphoomu baatooshshi Lemiina Shoolu (24) agani damoozinni roora dinosi.

4. Lame doorshu dironna hakkuy aleenni owaatino Qoqqowu Pirezidantichira hattee yannara rooru biirote sooreeyye horonsidhanno gedee kaameela qoqqowu mootimmate bajeettenni hirre uynanni.

5. Konni quwira cinaancho quwa 2 (a) aana worroonniri hee’rirono kaameela hirre uynanni soooreeyyera kaameelu baatooshshe afi’rate qoosso diheedhannonsa.

**10. Meessi Keeri Agarooshshi Owaante**

Pirezidatichu woy 2ki pirezidantichi woy konni deerrinni mootoo’mitinori biilloonyu aana noo yannara meessinsa keeri agarooshshe assinanni sa’noonniha ikkiro biillonyunni ka’uro

ላይ የሚገኙ የመንግሥት ተሿሚዎች፤ የሬጂኦፖሊታን ከተማ ምክትል ከንቲባ ወይም በተመሳሳይ ደረጃ ላይ ለሚገኙ የመንግሥት ተሿሚዎች የመነሻ ክፍያው የሦስት (3) ወራት ያልተጣራ ደመወዝ ሆኖ ከአንድ የምርጫ ዘመን በላይ ላለው ለእያንዳንዱ ተጨማሪ የአንድ የአንድ ዓመት አገልግሎት የአንድ (1) ወር ያልተጣራ ደመወዝ ክፍያ እየታከለ የሚሰላ ሲሆን ከሁለት የምርጫ ዘመን በላይ ላለው ለእያንዳንዱ ተጨማሪ አንድ ዓመት አገልግሎት የሁለት ወር (2) ወር ያልተጣራ ደመወዝ እየተጨመረ ይከፈላል፤

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) ከፊደል ተራ (ሀ-መ) ሥር የተደነገገው ቢኖርም፣ ለተሽከርካሪ አበል የሚከፈለው ክፍያ ከሃያ አራት (24) ወራት ደመወዝ መብለጥ የለበትም::

4. ሁለት የምርጫ ዘመንና ከዚያ በላይ ላገለገለ ርዕሰ መስተዳደር በወቅቱ አብዛኛዎቹ የቢሮ ኃላፊዎች የሚጠቀሙበት ዓይነት ተሽከርካሪ በክልሉ መንግሥት በጀት ተገዝቶ ይሰጣል::

5. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 (ሀ) ስር የተደነገገዉ ቢኖርም መኪና ተገዝቶ የሚሰጣቸዉ ኃላፊዎች የተሽከርካሪ አበል የማግኘት መብት አይኖራቸዉም::

**10. የግል ደህንነት ጥበቃ አገልግሎት**

ፕሬዚዳንት ወይም ምክትል ፕሬዚዳንት ወይም በተመሳሳይ ደረጃ ላይ የሚገኙ የመንግሥት ተሿሚዎች በኃላፊነት ላይ በነበሩበት ወቅት የግል ደህንነት ጥበቃ ይደረግላቸው የነበረ

agarooshshu wolqa lamu (2) manninni ajjannokkita gaammanninsa.

**12. Owaantete Taje Woraqata**

1. Biilloonyunni Ka'ino Mootimmate Jeefisiisaano Gaamo Miillara Owaantete Taje Woraqata uynannihu aane noo garinni ikkanno:-

a) Lamu doorshu dirira woy hakkuy aleenni loosinoha ikkiro umikki deerri tajete woraqatu uynannisi;

b) Mittu doorshu diri aleenninna lamu doorshu diri woroonni owaatinoha ikkiro layinki deerri tajete woraqata uynannisi;

c) Mitto wo'ma doorshu diro loosinoha ikkiro 3ki deerri tajete woraqatu uynannisi;

d) Mittu doorshu diri bocu diri aleenna mittu doorshu diri woroonni loosinoha ikkiro 4ki deerri tajete woraqata uynannisi.

2. Pirezidantichu, 2ki pirezidantichi woy konni deerrinni mootoo'mitinorira, amaalete mini songaafichira, biirote sooreessira, rejiopolitanete quchumi kantiiwira, zoonete qaru gashshaanchira, komishiinerete, qara dayrekiterera, 2ki biirote sooreessira, rejiopolitanete quchumi 2ki kantiiwira woy

እንደሆነ ከኃላፊነት ሲነሱም ከሁለት ሰዉ የማያንስ የጥበቃ ኃይል ይመደብላቸዋል፡፡

**12. የአገልግሎት የምስክር ወረቀት**

1. ከኃላፊነት ለተነሡ የሕግ አስፈፃሚ ምድብ አባላት የአገልግሎት ምስክር ወረቀት የሚሰጠዉ እንደሚከተለዉ ይሆናል፡-

ሀ) ሁለት የምርጫ ዘመን ወይም ከዚያ በላይ ያገለገለ ከሆነ አንደኛ ደረጃ የአገልግሎት የምስክር ወረቀት ይሰጠዋል፤

ለ) ከአንድ የምርጫ ዘመን በላይ እና ከሁለት የምርጫ ዘመን በታች ያገለገለ ከሆነ ሁለተኛ ደረጃ የአገልግሎት የምስክር ወረቀት ይሰጠዋል፤

ሐ) አንድ ሙሉ የምርጫ ዘመን ያገለገለ ከሆነ ሶስተኛ ደረጃ የአገልግሎት የምስክር ወረቀት ይሰጠዋል፤

መ) ከአንድ የምርጫ ዘመን ግማሽ በላይና ከአንድ የምርጫ ዘመን በታች ያገለገለ ከሆነ አራተኛ ደረጃ የአገልግሎት የምስክር ወረቀት ይሰጠዋል፤

2. ፕሬዚዳንት፣ ምክትል ፕሬዚዳንት ወይም በተመሳሳይ ደረጃ ላይ ለሚገኙ የመንግሥት ተሿሚዎች፣ ለምክር ቤት አፈ ጉባኤ፣ ምክትል አፈ ጉባኤ፣ ለጽህፈት ቤት ኃላፊ፣ ለቢሮ ኃላፊ፣ ለሬጂኦፖሊታን ከተማ ከንቲባ፣ ለዞን ዋና አስተዳዳሪ፣ ለኮሚሽነር፣ ለዋና ዳይሬክተር፣ ለምክትል ቢሮ ኃላፊ፣ ለሬጂኦፖሊታን ከተማ ምክትል ከንቲባ ወይም

konni deerrinni mootoo’mitinorira uynanni owaantete taje woraqatira qoqqowu pirezidantichinna qoqqowu amaalete mini songaafichi malaatissannoha ikkanno.

3. Ayno owaantete taje woraqata uynoonnisihu:-

a) Mootimmate fayyimma uurrinshara xagisi’rate uynanni owaantera balaxo afi’rano;

b) Dagate gambooshshi hee’rannowa ayirrinyu baycho uynannisi.

4. Umikki deerri tajete woraqata uynoonnisihu pirezidantichi, 2ki pirezidantichi woy konni deerrinni mootoo’mitinori konne quwa cinaancho quwa 3 hunda seerroonni qoossonna horo gobbaanni ledamannore hajo la’anno bisi ledo amaalamatenni;-

a) Diplomatikete paasipoorte uynannisi gede assinanni;

b) Horophilu fooliishshi’ranno basera baxxino ayirrinye (VIP) afi’ranno gede assinanni;

c). Horophilunni gobbate giddo ha’rinsho assanno yannara tikeetete baatooshshe 50% anga mootimmatenni baantanniha ikkanno.

5. Layinki deerri owaantete taje woraqata uynoonni pirezidantichi, 2ki pirezidantichi woy konni deerri owaantete taje woraqata uynonnisihu biirote sooreessi, rejiopolitanete quchumi kantiiwi, zoonete

በተመሳሳይ ደረጃ ላይ ለሚገኙ የመንግሥት ተሿሚዎች የሚሰጥ የአገልግሎት የምስክር ወረቀት በክልሉ መንግሥት ፕሬዚዳንት እና በክልሉ ምክር ቤት አፌ ጉባኤ የሚፈረም ይሆናል፤

3. ማንኛውም የአገልግሎት የምስክር ወረቀት የተሰጠው ባለመብት፡-

ሀ) በመንግሥት የጤና ተቋም ውስጥ የሚሰጠውን የህክምና አገልግሎት ቅድሚያ ያገኛል፤

ለ) በሕዝባዊ ስብሰባዎች ላይ የክብር ቦታ ይሰጠዋል፤

4. አንደኛ ደረጃ የአገልግሎት የምስክር ወረቀት የተሰጠው ፕሬዚዳንት፣ ምክትል ፕሬዚዳንት ወይም በተመሳሳይ ደረጃ ላይ የሚገኝ የመንግሥት ተሿሚ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) ሥር ከተደነገጉት መብት እና ጥቅሞች በተጨማሪ ጉዳዩ ከሚመለከተው አካል ጋር በመመካከር፡-

ሀ) ዲፕሎማቲክ ፓስፖርት እንዲሰጠው ይደረጋል፤

ለ) በአውሮፕላን ማረፊያ ልዩ የክብር አገልግሎት (VIP) እንዲያገኝ ይደረጋል፤

ሐ) በአየር የአገር ውስጥ በረራ ሲያደርግ የአየር ቲኬቱ ዋጋ ሃምሳ በመቶ (50%) በመንግሥት የሚሸፈን ይሆናል፤

5. ሁለተኛ ደረጃ የአገልግሎት የምስክር ወረቀት የተሰጠው ፕሬዚዳንት፣ ምክትል ፕሬዚዳንት ወይም በተመሳሳይ ደረጃ ላይ የሚገኙ የመንግሥት ተሿሚዎች ወይም አንደኛ ደረጃ የአገልግሎት የምስክር ወረቀት የተሰጠው የቢሮ ኃላፊ፣ የሬጂኦፖሊታን ከተማ ከንቲባ፣ የዞን ዋና

qaru gashshaanchi woy konni deerrira mootoonsinoonniri konni quwa cinaancho quwa (3) hunda seerroonni qoossonna horo gobbaanni ledamannore hajo la'anno bissa ledo amaalamatenni:-

a) Dipilomatikete paasipoorte uynannisi gede assinanni;

b) Horophilu dirrannowa baxxinoha ayirrinye /VIP/ afi'ranno gede assinanni;

C. Horophilunni gobbate giddo ha'rinsho assanno wote tikeetete baatooshshe 25% mootimmatenni baantanniha ikkanno.

6. Sayikki deerri owaantete taje woraqata uynoonni pirezidantichi, 2ki pirezidantichi woy konni deerrinni mootoonsinoonniri woy 2ki deerriha owaantete taje woraqata uynoonnisi biirote sooreessi, rejiopolitanete quchumi kantiiwi zoonete qaru gashshaanchi woy konni deerrinni mootoonsinoonniri woy 1ki deerrira owaantete taje woraqata uynoonni komishiinere, qaru dayrekitereichi, 2ki biirote sooreessi, rejopolitanete quchumi 2ki kantiiwi woy konni deerrinni mootoonsinoonniri konni quwira cinaancho quwa (3) hunda seerroonni qoossonna horo gobbaanni ledamannore hajo la'annonsa bissa ledo amaalamatenni;-

a) Diplomatikete paasiporte uynannisi gede assinnanni;

b) Horophilu fooliishshi'rannowa baxxinno

አስተዳዳሪ ወይም በተመሳሳይ ደረጃ ላይ የሚገኝ የመንግሥት ተሿሚ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) ሥር ከተደነገጉት መብት እና ጥቅሞች በተጨማሪ ጉዳዩ ከሚመለከተው አካል ጋር በመመካከር፡-

ሀ) ዲፕሎማቲክ ፓስፖርት እንዲሰጠው ይደረጋል፤

ለ) በአውሮፕላን ማረፊያ ልዩ የክብር አገልግሎት (VIP) እንዲያገኝ ይደረጋል፤

ሐ) በአየር የአገር ውስጥ በረራ ሲያደርግ የአየር ቲኬቱ ዋጋ ሃያ አምስት በመቶ (25%) በመንግሥት የሚሸፈን ይሆናል፤

6. ሶስተኛ ደረጃ የአገልግሎት የምስክር ወረቀት የተሰጠው ፕሬዚዳንት፣ ምክትል ፕሬዚዳንት ወይም በተመሳሳይ ደረጃ ላይ የሚገኙ የመንግሥት ተሿሚዎች ወይም ሁለተኛ ደረጃ የአገልግሎት የምስክር ወረቀት የተሰጠው የቢሮ ኃላፊ፤ ሬጂኦፖሊታን ከተማ ከንቲባ፣ የዞን ዋና አስተዳዳሪ ወይም በተመሳሳይ ደረጃ ላይ የሚገኙ የመንግሥት ተሿሚዎች ወይም አንደኛ ደረጃ የአገልግሎት የምስክር ወረቀት የተሰጠው ኮሚሽነር፣ ዋና ዳይሬክተር፣ ምክትል የቢሮ ኃላፊ፣ ሬጂኦፖሊታን ከተማ ምክትል ከንቲባ ወይም በተመሳሳይ ደረጃ ላይ የሚገኝ የመንግሥት ተሿሚ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) ሥር ከተደነገጉት መብት እና ጥቅሞች በተጨማሪ ጉዳዩ ከሚመለከተው አካል ጋር በመመካከር፡-

ሀ) ዲፕሎማቲክ ፓስፖርት እንዲሰጠው ይደረጋል፤

ለ) በአውሮፕላን ማረፊያ ልዩ የክብር አገልግሎት

ayirinye (VIP) afi'ranno gede assinanni;

C. Horophilunni gobbate giddo assanno ha'rinshora tikeetete baatooshshe 10% mootimma baattanno;

7. Shoolki deerri owaantete taje woraqata uynoonni pirezidantichi, $2^{ki}$ pirezidantichi woy konni deerrinni mootoonsinoonniri woy $3^{ki}$ deerriha owaantete taje woraqata uynoonnisi biirote sooreessi, rejiopolitaanete quchumi kantiiwi, zoonete qaru gashshaanchi woy konni deerrinni mootoonsinoonniri woy $2^{ki}$ deerrira owaantete taje woraqa uynoonni komishiinre, qaru dayrekiterichi, $2^{ki}$ biirote sooreessi, rejopolitaanete quchumi $2^{ki}$ kantiiwi woy konni deerrinni mootoonsinoonniri konni quwira cinaancho quwa (3) hunda seerroonni qoossonna horo hajo la'annonsa bissa ledo malamatenni;-

a) Dipilomatete paasiporte uynannisi gede assinanni;

b) Horophilu fooliishshi'rannowa baxxitino ayirrinye (VIP) afi'ranno gede assinanni.

8. Shoolki deerriha owaantete taje woraqata uynoonnisi biirote sooreessi, rejiopolitaanete quchumi kantiiwi, zoonete qaru gashshaanchi woy konni deerrinni mootoonsinoonniri woy $3^{ki}$ deerriha owaantete taje woraqata uynoonni

(VIP) እንዲያገኝ ይደረጋል፤

ሐ) በአየር የአገር ውስጥ በረራ ሲያደርግ የአየር ቲኬቱ ዋጋ አሥር በመቶ (10%) በመንግሥት የሚሸፈን ይሆናል፤

7. አራተኛ ደረጃ የአገልግሎት የምስክር ወረቀት የተሰጠው ፕሬዚዳንት ወይም ምክትል ፕሬዚዳንት እና በተመሳሳይ ደረጃ ላይ የሚገኙ የመንግሥት ተሿሚዎች ወይም ሶስተኛ ደረጃ የአገልግሎት የምስክር ወረቀት የተሰጠው የቢሮ ኃላፊ፤ ለሬጂኦፖሊታን ከተማ ከንቲባ፣ የዞን ዋና አስተዳዳሪ እና በተመሳሳይ ደረጃ ላይ የሚገኙ የመንግሥት ተሿሚዎች ወይም ሁለተኛ ደረጃ የአገልግሎት የምስክር ወረቀት የተሰጠው ኮሚሽነር፣ ዋና ዳይሬክተር፣ ምክትል የቢሮ ኃላፊ፤ የሬጂኦፖሊታን ከተማ ምክትል ከንቲባ እና በተመሳሳይ ደረጃ ላይ የሚገኝ የመንግሥት ተሿሚ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) ስር ከተደነገጉት መብት እና ጥቅሞች በተጨማሪ ጉዳዩ ከሚመለከተው አካል ጋር በመመካከር፡-

ሀ) ዲፕሎማቲክ ፓስፖርት እንዲሰጠው ይደረጋል፤

ለ) በአውሮፕላን ማረፊያ ልዩ የክብር አገልግሎት (VIP) እንዲያገኝ ይደረጋል፤

8. አራተኛ ደረጃ የአገልግሎት የምስክር ወረቀት የተሰጠው የቢሮ ኃላፊ፤ የሬጂኦፖሊታን ከተማ ከንቲባ፣ የዞን አስተዳዳሪ ወይም በተመሳሳይ ደረጃ ላይ የሚገኙ የመንግሥት ተሿሚዎች ወይም ሶስተኛ ደረጃ የአገልግሎት የምስክር ወረቀት የተሰጠው ኮሚሽነር፣ ዋና ዳይሬክተር፣ ምክትል

komishiinere, qaru dayrekiterichi, 2[ki] biirote sooreessi, rejopolitanete quchumi 2[ki] kantiiwi woy konni deerrinni mootoonsinoonniri konni quwira cinaancho quwa (3) hunda seerronni qoossonna horo lende hajo la'annonsa bissa ledo malamatenni servisete paaspoorte uynannisi gede assinanni;

9. Shoolki deerri owaantete taje woraqata uynoonnisihu komishiinere, qaru dayrekiterichi, 2[ki] biirote sooreessi rejiopolitanete quchumi 2[ki] kantiiwi woy konni deerrinni mootoonsinoonniri konni quwira cinaancho quwa (3) hunda seerroonni qoossonna horo afidhanno.

**13. Tenne Kalqenni Rewootenni Baxxino Qoossaanchi Qoossonna Horo**

1. Biilloonyunni Ka'ino Mootimmate Jeefisiisaano Gaamo Miillara loosu aana heedhe rewootenni baxxituro;-
   a) Rewoote ledo amadaminohunni addi addi fulo baatate sasu (3) agani damooza maatete baantanni;
   b) Biilloonyunni kaiha ikkiro baantara hasiissannoha umo dandaate baatooshshe, biilloonyunni geegiissate baatooshshe, gallanni mini baatooshshenna kaameelu baatooshshe maatete baantanni.
2. Pirezidantichu, 2[ki] pirezidantichi, biirote sooreessi, rejiopolitanete quchumi kantiiwi, zoonete qaru gashshaanchi, komishiinere, qaru

የቢሮ ኃላፊ፤ ሬጂኦፖሊታን ከተማ ምክትል ከንቲባ ወይም በተመሳሳይ ደረጃ ላይ የሚገኝ የመንግሥት ተሿሚ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) ሥር ከተደነገጉት መብት እና ጥቅሞች በተጨማሪ ጉዳዩ ከሚመለከተው አካል ጋር በመመካከር ሰርቪስ ፓስፖርት እንዲሰጠው ይደረጋል፤

9. አራተኛ ደረጃ የአገልግሎት የምስክር ወረቀት የተሰጠው ኮሚሽነር፣ ዋና ዳይሬክተር፣ ምክትል የቢሮ ኃላፊ፤ ለሬጂኦፖሊታን ከተማ ምክትል ከንቲባ ወይም በተመሳሳይ ደረጃ ላይ የሚገኙ የመንግሥት ተሿሚዎች በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) ሥር የተደነገጉትን መብት እና ጥቅሞች ያገኛሉ፡፡

**13. ከዚህ ዓለም በሞት የተለየ ባለመብት መብትና ጥቅሞች**

1. ከኃላፊነት ለተነሡ የሕግ አስፈፃሚ ምድብ አባላት ከዚህ ዓለም በሞት ቢለይ እንደሚከተለዉ ይስተናገዳል፡-
   ሀ) ከሞቱ ጋር ተያይዞ የሚወጡ ወጪዎችን ለመሸፈን የሶስት (3) ወር ያልተጣራ ደመወዝ ለቤተሰቡ ይከፈላል፤
   ለ) ከኃላፊነት ቢነሳ ኖሮ ሊከፈለው ይገባ የነበረው የመቋቋሚያ አበል፤ የኃላፊነት ስንብት ክፍያ፤ የመኖሪያ ቤት አበልና የተሽከርካሪ አበል ለቤተሰቡ ይከፈላል፤
2. ፐሬዚዳንት፣ ምክትል ፐሬዚዳንት፣ የቢሮ ኃላፊ፣ ሬጂኦፖሊታን ከተማ ከንቲባ፣ ለዞን ዋና አስተዳዳሪ፣ ኮሚሽነር፣ ዋና ዳይሬክተር፣

dayrekiterichi, 2ki biirote sooreessi woy konni deerrinni mootoonsinoonniri rejiopolitanete quchumi 2ki kantiiwi woy konni deerrinni mootoonsinoonniri horo afir'ate albaanni rewootenni baxxituro baantara hasiisannoha umo dandaate baatooshshe, biillonyunni geegiissate baatooshshe, gallanni mini baatooshshenna kaameelu baatooshshe maatete baantanni.

3. Pirezidantichu, 2ki pirezidantichi woy konni deerrira afantanno mootimmate biilto loosu aana heedhe woy sooreessimmatenni ka'e tenne kalqenni rewootenni baxxituha ikkiro:-

   a) Reewoosi garanna heeshshosi dhagge mootimmate tuqu xaadooshshinni kullanni;
   b) Madaarshu amanyooti qoqqowu maarshi baandenninna ayirrinyu dukkisonni jeefamanno;
   c) Qoqqowu albisaano mootimmate biilto madaarshu amanyooti aana leellatenni daraarcho worate amanyoote jeefissanno;
   d) Madaarshu amanyooti madaarsha jeefissannorinni ikke tenne hajora fulo mootimmatenni ikkitanno.

14. **Qoqqowu Seeru Allaalaano**

Konni Lallawira quwa 35 kayse 40 geeshsha noohu xaphoomu yoo mini yooaanonna aliidi yoo mini pirezidantoota la'anno seerubba qoqqowu farcote biirora noo seeru allalaanora jeefinsantannota ikkitanno.

ምክትል የቢሮ ኃላፊ ወይም በተመሳሳይ ደረጃ ላይ የሚገኙ የመንግሥት ተሿሚዎች፤ ሬጂኦፖሊታን ከተማ ምክትል ከንቲባ ወይም በተመሳሳይ ደረጃ ላይ የሚገኝ የመንግሥት ተሿሚ ጥቅሞችን ከማግኘቱ በፊት ከዚህ ዓለም በሞት ቢለይ ሊከፈለው ይገባ የነበረው የመቋቋሚያ አበል፤ የኃላፊነት ስንብት ክፍያ፤ የመኖሪያ ቤት አበልና የተሽከርካሪ አበል ለቤተሰቡ ይከፈላል፤

3. ፕሬዚዳንት፣ ምክትል ፕሬዚዳንት ወይም በተመሳሳይ ደረጃ ላይ የሚገኝ የመንግሥት ተሿሚ በሥራ ላይ እያለ ወይም ከኃላፊነት ተነስቶ ከዚህ ዓለም በሞት የተለየ እንደሆነ፡-

   ሀ) ዜና እረፍቱና የህይወት ታሪኩ በመንግሥት ሚዲያ ይነገራል፤
   ለ) የቀብር ሥነ-ሥርዓቱ የክልሉ ማርሽ ባንድና የክብር ዘብ በተገኘበት ይፈጸማል፤
   ሐ) የክልሉ ከፍተኛ የመንግሥት ባለሥልጣን በቀብር ሥነ-ሥርዓቱ ላይ በመገኘት የአበባ ጉንጉን የማስቀመጥ ሥነ-ሥርዓት ይፈጽማል፤
   መ) የቀብር ሥነ-ሥርዓቱ በቀብር አስፈጻሚዎች የሚፈጸም ሆኖ ለዚህ የሚውል ወጪ በመንግሥት የሚሸፈን ይሆናል፡፡

14. **ስለ ክልል ዐቃቢያነ ሕግ**

በዚህ አዋጅ ከአንቀጽ 35 እስከ 40 ያሉት የጠቅላይ ፍርድ ቤት ዳኞችንና የከፍተኛ ፍርድ ቤት ፕረዚዳንቶችን የሚመለከቱ ድንጋጌዎች በክልል ፍትህ ቢሮ ደረጃ ላሉ ዐቃቢያነ ሕግ ላይም ተፈፃሚነት ይኖረዋል፡፡

## Gafa Sase

### Biilloonyunni Ka'ino Seera Fushshitanno Bissa Biilto Qoossonna Horo

**15.Wommete Qoosso**

1. konni Lalawi quwa 5 hunda seerroonni wommete qoosso Amaale Mini songaafichira, layinki songaafichira, uurrinshu komite ganbisaanchira, uurrinshu komite layinki ganbisaanchira, borrote mini sooressira woy rejiopolitanete quchumi songaafichira, rejiopolitanete quchumi 2ki songaafichira woy konni deerrira mootoonsinoonnirira jeefishshu hee'rannosi.

2. Wommete qoosso la''annosi seeri garinni jeeffannota ikkitanno.

**16. Umo Dandaate Baatooshshe**

1. konni Lalawi quwa 6 hunda seerroonni umo dandaate baatooshshi Amaalete Mini songaafichira, layinki songaafichira, uurrinshu komite ganbisaanchira, uurrinshu komite layinki ganbisaanchira, borrote mini sooressira, rejiopolitaanete quchumi songaafichira, rejiopolitaanete quchumi 2ki songaafichira woy konni deerrira mootoonsinoonnirira jeefishshu hee'rannosi..

2. Ayno qoqqowu Amaale Mini miila ikke mitto doorshu diro gude biilloonyunni kairo Amaalete Mini 2ki songaafichira baantanniha xeinsoonnikkiha aganu damooza 5 (Ontu) aganiha daaragootete daninni uynannisi.

## ክፍል ሦስት

### ከኃላፊነት የተነሱ የሕግ አውጪ አካላት ኃላፊዎች መብቶችና ጥቅሞች

**15. የጡረታ መብት**

1. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 5 ሥር የተደነገገው የጡረታ መብት ለምክር ቤቱ አፈ-ጉባኤ፣ ምክትል አፈ-ጉባኤ፣ ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ፤ ቋሚ ኮሚቴ ምክትል ሰብሳቢ፤ ጽህፈት ቤት ኃላፊ ወይም የሬጂኦፖሊታን ከተማ አፈ-ጉባኤ፣ ምክትል አፈ-ጉባኤ ወይም በተመሳሳይ ደረጃ ላይ ላሉ የመንግሥት ተሿሚዎች ተፈጻሚነት ይኖረዋል፤

2. የጡረታ መብት በሚመለከተው ህግ መሠረት የሚፈጸም ይሆናል።

**16. የመቋቋሚያ አበል**

1. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 6 ሥር የተደነገገው የመቋቋሚያ አበል ለምክር ቤቱ አፈ-ጉባኤ፣ ምክትል አፈ-ጉባኤ፣ ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ፤ ቋሚ ኮሚቴ ምክትል ሰብሳቢ፣ ጽህፈት ቤት ኃላፊ ወይም የሬጂኦፖሊታን ከተማ አፈ-ጉባኤ፣ ምክትል አፈ-ጉባኤ ወይም በተመሳሳይ ደረጃ ላይ ላሉ የመንግሥት ተሿሚዎች ተፈጻሚነት ይኖረዋል፤

2. ማንኛውም የክልል ምክር ቤት አባል አንድ የምርጫ ዘመን አጠናቅቆ ከኃላፊነት ሲነሳ ለምክር ቤት ምክትል አፈ- ጉባኤ የሚከፈለውን ያልተጣራ ወርሃዊ ደመወዝ የአምስት (5) ወራት በዳረጎት መልክ ይሰጠዋል፤

3, Aleenni cinaancho quwa 2 aana xawinsoonnihu noo gedeenni hee’reenna mittu mittunku doorshu dirira mittu agani xeinsoonnikki damoozinni boco (½) lende shallange baantanniha ikkanno.

**17. Biilloonyunni Geegiissate Baatooshshe**

1. Konni Lallawira quwa 7 hunda seerroonni biilloonyunni geegiissate baatooshshi Amaalete Mini songaafichira, layinki songaafichira, uurrinshu komite ganbisaanchira, uurrinshu komite layinki ganbisaanchira, borrote mini sooreessira, rejiopolitanete quchumi songaafichira, rejiopolitanete quchumi $2^{ki}$ songaafichira woy konni deerrinni mootoo’mitinorira jeefishshu hee’rannosi.

**18. Gallanni Mini Awallenna Hee’nanni Mine**

1. Amaalete Mini songaafichira, layinki songaafichira, uurrinshu komite ganbisaanchira, uurrinshu komite layinki ganbisaanchira, borrote minni sooreessira rejiopolitanete quchumi songaafichira, rejiopolitanete quchumi $2^{ki}$ songaafichira woy konni deerrinni mootoo’mitinori hee’nanni mini baatooshshe baantannihu:-

   a) Ajay ajeenna mittu doorshu diri owaante ee biilloonyunni kairo; woy

   b) Bocu doorshu dirinni ajjinokki owaante owaate xissote, bisu gawajjonni woy wolqate alee ikkino wolu korkaatinni biilloonyunni kairo gallanni mini baatooshshe baantannisi.

3. ከላይ በንዑስ አንቀጽ 2 ላይ የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ ከአንድ የምርጫ ዘመን በላይ ላለው ለእያንዳንዱ ምርጫ ዘመን ከአንድ ወር ካልተጣራ ደመወዝ 1/2 (አንድ ሁለተኛ) ክፍያ እየታከለ የሚሰላ ይሆናል፡፡

**17. የኃላፊነት ስንብት ክፍያ**

በዚህ አዋጅ አንቀጽ 7 ሥር የተደነገገው የኃላፊነት ስንብት አበል ለምክር ቤቱ አፈ-ጉባኤ፣ ምክትል አፈ-ጉባኤ፣ ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ፤ ቋሚ ኮሚቴ ምክትል ሰብሳቢ፤ ጽህፈት ቤት ኃላፊ፣ የሬጂኦፖሊታን ከተማ አፈ-ጉባኤ፣ ምክትል አፈ-ጉባኤ ወይም በተመሳሳይ ደረጃ ላይ ላሉ የመንግሥት ተሿሚዎች ተፈጻሚነት ይኖረዋል፡፡

**18. የመኖሪያ ቤት አበል እና የመኖሪያ ቤት**

1. ለምክር ቤቱ አፈ-ጉባኤ፣ ምክትል አፈ-ጉባኤ፣ ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ፤ ቋሚ ኮሚቴ ምክትል ሰብሳቢ፤ ጽህፈት ቤት ኃላፊ፣ ሬጂኦፖሊታን ከተማ አፈ-ጉባኤ፣ ምክትል አፈ-ጉባኤ ወይም በተመሳሳይ ደረጃ ላይ ላሉ የመንግሥት ተሿሚዎች የመኖሪያ ቤት አበል የሚከፈለዉ፡-

   ሀ) ቢያንስ አንድ የምርጫ ዘመን አገልግሎ ከኃላፊነት ከተነሳ፤ ወይም

   ለ) ከግማሽ የምርጫ ዘመን ያላነሰ አገልግሎ በህመም፤ በአካል ጉዳት ወይም ከአቅም በላይ በሆነ ሌላ ምክንያት ከኃላፊነት ከተነሳ የመኖሪያ ቤት አበል ይከፈለዋል፤

2. Konni Lallawira quwa 8 cinaancho quwa 2 (a) hunda seerroonni gallanni mini baatooshshi Amaalete Mini songaafichiranna $2^{ki}$ songaafichira jeefinsanniha ikkanno.

3. Konni lallawira quwa 8 cinaancho quwa 2(b) hunda seerroonni gallanni mini baatooshshi amaalete mini uurrinshu komite ganbisaanchira, amaalete mini borro mini soorreessira, rejopolitanete quchumi songaafichira woy konni deerrira mootoo'mitinorira jeefamannoha ikkanno.

4. konni lallawira quwa 8 cinaancho quwa 2 (c) hunda seerroonnihu gallanni mini baatooshshi amaalete mini uurrinshu komite $2^{ki}$ ganbisaanchira, rejiopolitaanete quchumi layinki songaafichira woy konni deerrira mootoo'mitinorira jeefishshu hee'rannosi.

5. Konni quwira cinaancho quwa 2-4 geeshsha seerroonniri hee'rirono gallanni minira baantanni xaphoomu baatooshshi lemiina shoolu (24) agani damooza roora dinosi.

**19. Kaameelu Baatooshshe**

1. Amaalete mini songaafichira, layinki songaafichira, uurrinshu komite ganbisaanchira, uurrinshu komite layinki ganbisaanchira, borrote minni sooreessira, rejopolitanete quchumi songaafichira, rejopolitanete quchumi $2^{ki}$ songaafichira woy konni deerrinni mootoo'mitinorira:-

    a). Ajanna mitto doorshu diro owaate biiloonyunni kairo woy

2. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 8 ንዑስ አንቀጽ 2 (ሀ) ሥር የተደነገገው የመኖሪያ ቤት አበል ለምክር ቤቱ አፈ-ጉባኤ እና ምክትል አፈ-ጉባኤ ተፈፃሚነት ይኖረዋል፤

3. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 8 ንዑስ አንቀጽ 2 (ለ) ሥር የተደነገገው የመኖሪያ ቤት አበል ለምክር ቤቱ ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ፤ ለምክር ቤቱ ጽህፈት ቤት ኃላፊ፣ ለሬጂኦፖሊታን ከተማ አፈ-ጉባኤ ወይም በተመሳሳይ ደረጃ ላይ ላሉ የመንግሥት ተሿሚዎች ተፈፃሚነት ይኖረዋል፤

4. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 8 ንዑስ አንቀጽ 2 (ሐ) ሥር የተደነገገው የመኖሪያ ቤት አበል ለምክር ቤቱ ቋሚ ኮሚቴ ምክትል ሰብሳቢ፣ ሬጂኦፖሊታን ከተማ ምክትል አፈ- ጉባኤ ወይም በተመሳሳይ ደረጃ ላይ ላሉ የመንግሥት ተሿሚዎች ላይ ተፈፃሚነት ይኖረዋል፤

5. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2-4 ሥር የተደነገገው ቢኖርም፤ ለመኖሪያ ቤት የሚከፈለው ጠቅላላ ክፍያ ከሃያ አራት (24) ወራት ደመወዝ መብለጥ የለበትም፡፡

**19. የተሽከርካሪ አበል**

1. ለምክር ቤቱ አፈ-ጉባኤ፣ ምክትል አፈ-ጉባኤ፣ ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ፤ ቋሚ ኮሚቴ ምክትል ሰብሳቢ፤ ጽህፈት ቤት ኃላፊ፣ ሬጂኦፖሊታን ከተማ አፈ-ጉባኤ፣ ምክትል አፈ-ጉባኤ ወይም በተመሳሳይ ደረጃ ላይ ላሉ የመንግሥት የመንግሥት ተሿሚ፡-

    ሀ) ቢያንስ አንድ የምርጫ ዘመን አገልግሎ ከኃላፊነት ከተነሳ፤ ወይም

b) Mittu doorshu diri bocinni ajjinokki yanna owaate xibbunni, bisu gawajjonni woy wolqate aleenni ikkino wolu korkaatinni biilloonyunni kairo kaameelu baatooshhshe baantannisi.

2. Konni lallawira quwa 9 cinaancho quwa 2 (a) hunda seerroonni kaameelu baatooshshi amaalete mini songaafichira woy 2[ki] songaafichira jeefishshu hee’rannosi

3. Konni lallawira quwa 9 cinaancho quwa 2 (b) hunda seerroonnihu kaameelu baatooshshi amaalete mini uurrinshu komite ganbisaanchira, borrote mini sooreessira woy konni deerrinni mootoo’mitinorira jeefishshu hee’rannosi.

4. Konni lallawira quwa 9 cinaancho quwa 2 (c) hunda seerroonni kameelu baatooshshi amaalete mini uurrinshu komite 2[ki] ganbisaanchiranna rejopolitanete quchumi layinki songaafichira jeefishshu hee’rannosi.

5. Konni quwi cinaanchu quwa 2-4 geeshsha seerroonnihu noo gedee hee’reenna kaameelaho baantannihu xaphoomu baatooshshi lemiina shoolu (24) aganni damooza roora dinosi.

6. Konni lallawira quwa 2 (a) hunda seerroonniri noo geedee hee’renna lame doorshu dironna hakkunni aleenni owaante uyno Amaalete Mini songaafichira hattee yannara roore biirote sooreeyye horonsidhanno gedee otomobile qoqqowu mootimma bajeettenni hirre uynanni.

7. Konni quwira cinaancho quwa 6 aana

ለ) ከአንድ የምርጫ ዘመን ግማሽ ያላነሰ አገልግሎ በህመም፣ በአካል ጉዳት ወይም ከአቅም በላይ በሆነ ሌላ ምክንያት ከኃላፊነት ከተነሳ የተሽከርካሪ አበል ይከፈለዋል፤

2. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 9 ንዑስ አንቀጽ 2 (ሀ) ሥር የተደነገገው የተሽከርካሪ አበል ለምክር ቤቱ አፈ-ጉባኤ ወይም ምክትል አፈ-ጉባኤ ተፈፃሚነት ይኖረዋል፤

3. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 9 ንዑስ አንቀጽ 2 (ለ) ሥር የተደነገገው የተሽከርካሪ አበል ለምክር ቤቱ ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ፣ ለምክር ቤቱ ጽህፈት ቤት ኃላፊ ወይም በተመሳሳይ ደረጃ ላይ ላሉ የመንግሥት ተሿሚዎች ተፈፃሚነት ይኖረዋል፤

4. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 9 ንዑስ አንቀጽ 2 (ሐ) ሥር የተደነገገው የተሽከርካሪ አበል በምክር ቤቱ ቋሚ ኮሚቴ ምክትል ሰብሳቢ ለምክር ቤቱ ጽህፈት ቤት ኃላፊ ወይም ለሬጂኦፖሊታን ከተማ ምክትል አፈ-ጉባኤ ላይ ተፈፃሚነት ይኖረዋል፤

5. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2-4 ሥር የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ለተሽከርካሪ የሚከፈለው ጠቅላላ አበል ክፍያ ከሃያ አራት (24) ወራት ደመወዝ መብለጥ የለበትም፤

6. በዚህ ንዑስ አንቀጽ 2 (ሀ) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ሁለት የምርጫ ዘመንና ከዚያ በላይ ላገለገለ ለምክር ቤት አፈ ጉባኤ በወቅቱ አብዛኛዎቹ የቢሮ ኃላፊዎች የሚጠቀሙበትን አዉቶሞቢል ተሽከርካሪ በክልሉ መንግሥት በጀት ተገዝቶ ይሰጣል።

7. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 6 ስር የተደነገገዉ ቢኖርም

worroonniri hee’rirono kaameela hirre uynanni soooreeyyera kaameelu baatooshshe afi’rate qoosso diheedhannonsa.

**20. Meessisi Keeranchimma Agarooshshi Owaante**

Songaafichunna 2ki songaafichi biilloonyu aana noo yannara meessi hobbaate agarooshshe assinanni sa’noonniha ikkiro konni lallawi quwa 11 hunda seerroonniri jeefamannoha ikkanno.

**21. Hodhishshunna Uduunnu Kayishshi Baatooshshe**

1. Amaalete mini songaafichi, 2ki songaafichi, uurrinshu komite ganbisaanchi, uurrinshu komite layinki ganbisaanchi, borrote mini sooreessi loosu diri goofeenna qaesi higannoha ikkiro isiranna maatesira hoguwunna uduunnu kayishshi baatooshshe yannate noo hodhishshi bikki garinni baantannisi.
2. Konni quwira cinaanchu quwa 1 hunda seerroonni garinni qoosaanchu uulla hodhishsha horonsi’ra noosi.
3. Konni quwira cinaanchu quwa 2 hunda seerroonniri hee’rirono wolqate aleenni ikkitino ikkito xaadduha ikkiro horophillu hodhishsha horoonsi’ra dandaanno.
4. konni quwira cinaanchu quwi (1) hunda seerroonni garinni uduunnu kayishshi fulo baatooshshe umisi uduunne iillishi’rate uulla hodhishshi baatooshshira calla mitte kume (1000) kiilo giraame, galtesinna oososi ledo ikkiro mitto

መኪና ተገዝቶ የሚሰጣቸዉ ከኃላፊነት የተነሱ ተሿሚዎች የተሽከርካሪ አበል የማግኘት መብት አይኖራቸዉም፡፡

**20. የግል ደህንነት ጥበቃ አገልግሎት**

አፈ-ጉባኤ እና ምክትል አፈ-ጉባኤ በኃላፊነት ላይ በነበሩበት ወቅት የግል ደህንነት ጥበቃ ይደረግላቸው የነበረ ከሆነ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 11 ሥር በተደነገገው መሠረት ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

**21. የመጓጓዣ እና የጓዝ ማንሻ አበል** 21.

1. የምክር ቤቱ አፈ-ጉባኤ፣ ምክትል አፈ- ጉባኤ፤ ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ፤ ምክትል ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ፣ የጽህፈት ቤት ኃላፊ የሥራ ዘመኑ አጠናቅቆ ወደ ቀድሞ መኖሪያው የሚመለስ ከሆነ ለራሱና ለቤተሰቡ የመጓጓዣ እና የጓዝ ማንሻ አበል በወቅቱ የትራንስፖርት ተመን መሠረት ይከፈለዋል፤
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ሥር በተደነገገው መሠረት ባለመብቱ የየብስ ትራንስፖርት መጠቀም አለበት፤
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 ሥር የተደነገገው ቢኖርም ከአቅም በላይ የሆነ ሁኔታ ሲያጋጥም የአየር ትራንስፖርት መጠቀም ይችላል፤
4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ሥር በተደነገገው መሠረት የጓዝ ማንሻ ወጪ አበል የግል እቃዎችን ለማድረስ ለየብስ ትራንስፖርት ለአበል ብቻ የአንድ ሺህ (1,000) ኪሎ ግራም፣ ከባለቤቱና ከልጆቹ

kumenna onte xibbe (1500) kiilo giramenna mitte mittente oosora mitte xibbe (100) kiilo giraame fajjinara dandiinanni.

5. Umisi kaameela horoonsi'rannoha ikkiro nadaajetenna qiwaatete fulo kiilomeetirete xeertinyi garinni shallangeenna mootimma baattannoha ikkanno.

## 22. Owaantete Taje Woraqata

1. Biilloonyunni kainohu Amaale Mini songaafichi, $2^{ki}$ songaafichi, uurrinshu komite ganbisaanchi, uurrinshu komite $2^{ki}$ ganbisaanchi, borrote mini sooreessi woy rejopolitaanete quchumi songaafichi woy $2^{ki}$ songaafichira konni deerrinni mootoo'mitinorinna amaalete mini miili;-

   a) Lame doorshu diro woy hakkuy ale uyno owaantera umi deerriha tejete woraqata uynannisi.

   b) Mittu doorshu diri aleenninna lamu doorshu diri woroonni uyno owaantera layinki deerriha tejete woraqata uynannisi.

   c) Mittu doorshu dirira uyno owaantera sayikki deerriha tajete woraqata uynannisi.

   d) Bocu doorshu diri aleenna mittu doorshu diri wori owaantera shoolki deerriha owaante tajete woraqata uynannisi.

ጋር ከሆነ ደግሞ የአንድ ሺህ አምስት መቶ (1,500) ኪሎ ግራም እና ለእያንዳንዱ ልጅ አንድ መቶ (100) ኪሎ ግራም ሊፈቀድ ይችላል፤

5. በግል መኪናው የሚጠቀም ከሆነ የነዳጅና ቅባት ወጪ በኪሎ ሜትር ርቀት መሠረት ተሰልቶ በመንግሥት የሚሸፈን ይሆናል፡፡

## 22. የአገልግሎት የምስክር ወረቀት

1. ከኃላፊነት የተነሳ የምክር ቤቱ አፈ-ጉባኤ፣ምክትል አፈ-ጉባኤ፤ ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ፤ ቋሚ ኮሚቴ ምክትል ሰብሳቢ፤ የጽህፈት ቤት ኃላፊ፣ የሬጂኦፖሊታን ከተማ አፈ-ጉባኤ፣ ምክትል አፈ-ጉባኤ ወይም በተመሳሳይ ደረጃ ላይ ያለ የመንግሥት ተሿሚ እና የምክር ቤቱ አባል፡-

   ሀ) ሁለት የምርጫ ዘመን ወይም ከዚያ በላይ ላገለገለ አንደኛ ደረጃ የአገልግሎት የምስክር ወረቀት ይሰጠዋል፤

   ለ) ከአንድ የምርጫ ዘመን በላይ እና ከሁለት የምርጫ ዘመን በታች ላገለገለ ሁለተኛ ደረጃ የአገልግሎት የምስክር ወረቀት ይሰጠዋል፤

   ሐ) አንድ የምርጫ ዘመን ላገለገለ ሦስተኛ ደረጃ የአገልግሎት የምስክር ወረቀት ይሰጠዋል፤

   መ) ከግማሽ የምርጫ ዘመን በላይ እና ከአንድ የምርጫ ዘመን በታች ላገለገለ አራተኛ ደረጃ የአገልግሎት የምስክር ወረቀት ይሰጠዋል፤

2. Amaalete Mini songaafichira uynanni tajete woraqatira qoqqowu mootimma pirezidantichinni malaatisamannoha ikkanno.

3. Amaalete mini $2^{ki}$ songaafichira, uurrinshu komite ganbisaanchira, uurrinshu komite $2^{ki}$ ganbisaanchira, rejopolitanete quchumi songaafichira, $2^{ki}$ songaafichira woy konni deerrira mootoo'mitino biiltoranna amalete mini miillara uynanni tajete woraqatira amaale mini songaafichi malaatisannoha ikkanno.

4. Konni lallawira quwa 12 cinaancho quwa (3-7) seerroonni owaante tajete woraqati afisiisawo horo Amaalete Mini songaafichiranna $2^{ki}$ songaafichira jeefishshu hee'rannosi.

5. Konni lallawira quwa 12 (3) nna (5-8) noo cinaano quwubbara seerroonnihu owaantete tajete woraqati horo afisiisannohu uurrinshu komite ganbisaanchira, borrote mini sooreessira, rejopolitaanete quchumi songaafichira woy konni deerrira mootoo'mitinorira jeefamannoha ikkanno.

6) Konni lallawira quwa 12 (3), (6-9) hunda seerroonni owaantete taje woraqati afisiisanno horo uurrinshu komite $2^{ki}$ ganbisaanchira, rejopolitanete quchumi $2^{ki}$ songaafichiranna konni deerrinni mootoo'mitinorira jeefishshu hee'rannosi.

7. Konni lallawira quwa 12 cinaancho quwa 3 (a) nna (b) hunda seerroonni qoossuwanna horo Amaalete Mini miilirano jeefishshu hee'rannonsa.

2. ለምክር ቤቱ አፈ-ጉባኤ የሚሰጠው የአገልግሎት የምስክር ወረቀት በክልሉ መንግሥት ፕሬዚዳንት የሚፈረም ይሆናል፤

3. ለምክር ቤቱ ምክትል አፈ-ጉባኤ፤ ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ፤ ቋሚ ኮሚቴ ምክትል ሰብሳቢ፣ ጽህፈት ቤት ኃላፊ፣ ሬጂኦፖሊታን ከተማ አፈ-ጉባኤ፣ ምክትል አፈ-ጉባኤ ወይም በተመሳሳይ ደረጃ ላይ ላሉ የመንግሥት ተሿሚዎች እና ለምክር ቤቱ አባላት የሚሰጠው የአገልግሎት የምስክር ወረቀት በምክር ቤቱ አፈ-ጉባኤ የሚፈረም ይሆናል፤

4. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 12 ንዑስ አንቀጽ 3-7 ሥር የተደነገጉት የአገልግሎት የምስክር ወረቀት የሚያስገኛቸው ጥቅሞች ለምክር ቤቱ አፈ-ጉባኤ እና ምክትል አፈ-ጉባኤ ተፈፃሚነት ይኖረዋል፤

5. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 12 (3) እና ከ5-8 ባሉት ንዑሳን አንቀጾች ሥር የተደነገጉት የአገልግሎት የምስክር ወረቀት የሚያስገኛቸው ጥቅሞች ለቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ፤ ጽህፈት ቤት ኃላፊ ወይም ለሬጂኦፖሊታን ከተማ ምክር ቤት አፈ-ጉባኤ ተፈፃሚነት ይኖረዋል፤

6. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 12 (3)፣ (6-9) ሥር የተደነገጉት የአገልግሎት የምስክር ወረቀት የሚያስገኛቸው ጥቅሞች የምክር ቤቱ ቋሚ ኮሚቴ ምክትል ሰብሳቢ፣ ሬጂኦፖሊታን ከተማ ምክትል አፈ-ጉባኤ ወይም በተመሳሳይ ደረጃ ተሿሚዎች ላይ ተፈፃሚነት ይኖረዋል፤

7. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 12 ንዑስ አንቀጽ 3 (ሀ) እና (ለ) ሥር የተደነገጉት መብትና ጥቅሞች ለምክር ቤቱ አባልም ተፈፃሚነት ይኖራቸዋል፡፡

**23) Loosu Gaamooshshe**

1. Dooramate woy mootoo’mate albaanni mootimmate loosu mine woy mootimmate latishshu uurrinsha loosaasincho ikkinohu amaalete mini songaafichi, $2^{ki}$ songaafichi, uurrinshu komite ganbisaanchi, uurrinshu komite $2^{ki}$ ganbisaanchi, borrote mini sooreessi, rejopolitanete quchumi songaafichi, rejopolitanete quchumi $2^{ki}$ songaafichi woy konni deerrinni mootoo’mitinori albi loosira higate xa’mi’riro noo seeri garinni loosisira higanno gede woy alba loose saino base wolunni amadantinoha ikkiro taalo ikkitino loosu base aana gaamamanno assinanni .
2. Amaalete mini songaafichi, $2^{ki}$ songaafichi, uurrinshu komite ganbisaanchi, $2^{ki}$ uurrinshu komite ganbisaanchi, borrote mini sooreessi, rejopolitanete quchumi songaafichi, rejopolitanete quchumi $2^{ki}$ songaafichi woy konni deerrira mootoo’mitinori albi loosira woy mootimmate latishshu uurrinshara konni quwira cinaancho quwa 1 hunda seerroonni garinni gaamama dandaa hoogiro wolu mootimmate loosi mine woy mootimmate latishshi uurrinshara heedhanno fano loosu basera gaamamanno gede assinanni.
3. Amaalete mini songaafichi, $2^{ki}$ songaafichi, uurrinshu komite ganbisaanchi, uurrinshu komite $2^{ki}$ ganbisaanchi, borrote mini sooreessi, rejopolitanete quchumi songaafichi,

**23. የሥራ ምደባ**

1. ከመመረጡ ወይም ከመሾሙ በፊት የመንግሥት መሥሪያ ቤት ወይም የመንግሥት የልማት ድርጅት ሠራተኛ የነበረ የምክር ቤቱ አፈ-ጉባኤ፣ ምክትል አፈ-ጉባኤ፣ ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ፤ ቋሚ ኮሚቴ ምክትል ሰብሳቢ፣ የጽህፈት ቤት ኃላፊ፣ የሬጂኦፖሊታን ከተማ አፈ-ጉባኤ፣ የሬጂኦፖሊታን ከተማ ምክትል አፈ-ጉባኤ ወይም በተመሳሳይ ደረጃ ላይ ያለ የመንግሥት ተሿሚ ወደ ቀድሞ ሥራው ለመመለስ ከጠየቀ ባለው ህግ ላይ በመመሥረት ወደ ሥራው እንዲመለስ ወይም በፊት የነበረበት ቦታ የተያዘ ከሆነ በተመሳሳይ የሥራ ቦታ ላይ እንዲመደብ ይደረጋል፡፡
2. የምክር ቤቱ አፈ-ጉባኤ፣ ምክትል አፈ- ጉባኤ፣ ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ፤ ቋሚ ኮሚቴ ምክትል ሰብሳቢ፣ የጽህፈት ቤት ኃላፊ፣ የሬጂኦፖሊታን ከተማ አፈ-ጉባኤ፣ ምክትል አፈ-ጉባኤ ወይም በተመሳሳይ ደረጃ ላይ ያለ የመንግሥት ተሿሚ ቀድሞ በነበረበት የመንግሥት መሥሪያ ቤት ወይም የመንግሥት የልማት ድርጅት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ሥር በተደነገገው መሠረት መመደብ ካልቻለ በሌላ የመንግሥት መሥሪያ ቤት ወይም የመንግሥት የልማት ድርጅት ባለ ክፍት የሥራ ቦታ ላይ እንዲመደብ ይደረጋል፤
3. የምክር ቤቱ አፈ-ጉባኤ፣ ምክትል አፈ- ጉባኤ፤ ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ፤ ቋሚ ኮሚቴ ምክትል ሰብሳቢ፤ የጽህፈት ቤት ኃላፊ፣ የሬጂኦፖሊታን ከተማ አፈ-ጉባኤ፣ ምክትል አፈ-ጉባኤ ወይም

rejopolitanete quchumi 2ki songaafichi woy konni deerrinni mootoo'minohu amaalete mini miila ikke loosino diro gaamamino mootimmate loosu mine woy mootimmate latishshu uurrinsha giddo uyno owaante gede assine kiirre loosu rosicho amandannisi .

4. Konni quwira cinaancho quwa 1-3 hunda noo seerubba biilloonyunni amandanni basera jeefishshu dihee'rannonsa.

## 24. Tenne Kalqenni Rewote Baxxino Qoossanchi Qoossonna Horo

1. Amaalete mini songaafichi, 2ki songaafichi, uurrinshu komite ganbisaanchi, uurrinshu komite 2ki ganbisaanchi, borrote mini sooreessi, rejopolitanete quchumi songaafichi, rejopolitanete quchumi 2ki songaafichinna konni deerrinni mootoo'minohu loosu aana hee're tenne kalqenni rewootenni baxxiro;-

a) Rewosi ledo amadaminohunni fultanno woxu fulo diwate sasu (3) agani xeinsoonnikki damooza maatesira baantanni.

b) Biilloonyunni kainoha ikkoommero baantasira hasiisannoha umo dandaate baatooshshe, biilloonyunni geegiissate baatooshshe, gallanni mini baatooshshenna kaameelu baatooshshe maatesira baantanni.

2. Amaalete Mini songaafichi, 2ki songaafichi, uurrinshu komite ganbisaanchi, uurrinshu komite 2ki ganbisaanchi, borrote mini sooreessi, rejiopolitanete quchumi songaafichi,

በተመሳሳይ ደረጃ ላይ ያለ የመንግሥት ተሿሚ በምክር ቤቱ ውስጥ ያገለገለበት ዘመን በተመደበበት የመንግሥት መሥሪያ ቤት ወይም የመንግሥት የልማት ድርጅት ውስጥ እንደተሰጠ አገልግሎት ተቆጥሮ የሥራ ልምዱ ይያዝለታል፤

4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1-3 ሥር ያሉ ድንጋጌዎች በሹመት በሚያዙ ቦታዎች ላይ ተፈፃሚነት አይኖራቸውም፡፡

## 24. ከዚህ ዓለም በሞት ስለተለየ ባለመብት መብትና ጥቅሞች

1. የምክር ቤቱ አፈ-ጉባኤ፣ ምክትል አፈ-ጉባኤ፤ ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ፤ ቋሚ ኮሚቴ ምክትል ሰብሳቢ፤ የጽህፈት ቤት ኃላፊ፣ የሬጂኦፖሊታን ከተማ አፈ-ጉባኤ፣ የሬጂኦፖሊታን ከተማ ምክትል አፈ-ጉባኤ ወይም በተመሳሳይ ደረጃ ላይ ያለ የመንግሥት ተሿሚ በሥራ ላይ እያለ ከዚህ ዓለም በሞት ቢለይ፡-

ሀ) ከሞቱ ጋር ተያይዞ የሚወጡ ወጪዎችን ለመሸፈን የሶስት (3) ወራት ያልተጣራ ደመወዝ ለቤተሰቡ ይከፈላል፤

ለ) ከኃላፊነት ተነስቶ ቢሆን ኖሮ ሊከፈለው ይገባ የነበረው የመቋቋሚያ አበል፣ የኃላፊነት ስንብት ክፍያ፣ የመኖሪያ ቤት አበልና የተሽከርካሪ አበል ለቤተሰቡ ይከፈላል፤

2. የምክር ቤቱ አፈ-ጉባኤ፣ ምክትል አፈ-ጉባኤ፤ ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ፤ ቋሚ ኮሚቴ ምክትል ሰብሳቢ፤ የጽህፈት ቤት ኃላፊ ወይም የሬጂኦፖሊታን ከተማ

rejopolitanete quchumi 2ki songaafichi woy konni deerrira mootoo'minohu horo afi'rasira balaxe tenne kalqenni rewootenni baxxiro baantasira hasiissanno baatooshshe, biilloonyunni geegiissate baatooshshe, gallanni mini baatooshshenna kaameelu baatooshshe maatesira daaragootete daninni uynanni.

3. Amaalete mini songaafichi, 2ki songaafichi loosu aana hee're woy biilloonyunni kae tenne kalqenni rewootenni baxxiro;-

a) Fooliishshosi duduwonna heeshshosi dhagge mootimmate tuqu xaadooshshinni lallanbanni;

b) Madaarshisi amanyoote qoqqowu maarchingete baandenna ayirrinyu dukkisaano leeltinowa gumullanni;

c) Qoqqowunniti aliidi mootimmate biilto madaarshisi amanyooti aana leelte awawu gungune worate amanyootinni gumulamanno.

d) Madaarshisi amanyooti madaarshu jeefisaanonni jeefinsanniha ikke konnira hasiissanno woxu fulo mootimmate baajeetenni jeefinsanniha ikkanno.

**Gafa Shoole**

**Biilloonyunni Ka'inori Seera Tirtanno Bissa Sooreeyye Qoossonna Horo**

**Cinaancho Gafa Mite**

**Xaphoomu Yoo Mini Pirezidantichinna Layinki Pirezidantichi Qoossonna Horo**

**25. Wommete Qoosso**

Xaphoomu yoo mini pirezidantichinna layinki pireziadantichi wommete qoosso afidhannohu wommete seeri garinni ikkanno.

አፈ-ጉባኤ፣ የሬጂኦፖሊታን ከተማ ምክትል አፈ-ጉባኤ ወይም በተመሳሳይ ደረጃ ላይ ያለ የመንግሥት ተሿሚ ጥቅሞችን ከማግኘቱ በፊት ከዚህ ዓለም በሞት ቢለይ ሊከፈለው ይገባ የነበረው የመቋቋሚያ አበል፤ የኃላፊነት ስንብት ክፍያ፤ የመኖሪያ ቤት አበልና የተሽከርካሪ አበል ለቤተሰቡ በዳረጎት መልክ ይሰጣል፡፡

3. የምክር ቤቱ አፈ-ጉባኤ ወይም ምክትል አፈ-ጉባኤ በሥራ ላይ እያለ ወይም ከኃላፊነት ተነስቶ ከዚህ ዓለም በሞት ቢለይ፡-

ሀ) ዜና እረፍቱና የህይወት ታሪኩ በመንግሥት ሚዲያ ይነገራል፤

ለ) የቀብር ሥነ-ሥርዓቱ የክልሉ ማርችንግ ባንድና የክብር ዘብ በተገኘበት ይፈጸማል፤

ሐ) የክልሉ ከፍተኛ የመንግሥት ባለሥልጣን በቀብር ሥነ-ሥርዓቱ ላይ በመገኘት የአበባ ጉንጉን የማስቀመጥ ሥነ-ሥርዓት ይፈጽማል፤

መ) የቀብር ሥነ-ሥርዓቱ በቀብር አስፈጻሚዎች የሚፈጸም ሆኖ ለዚህ የሚውል ወጪ በመንግሥት የሚሸፈን ይሆናል፡፡

**ክፍል አራት**

**ከኃላፊነት የተነሱ የሕግ ተርጓሚ አካላት ኃላፊዎች መብት እና ጥቅሞች**

**ንኡስ ክፍል አንድ**

**የጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት እና ምክትል ፕሬዚዳንት መብት እና ጥቅሞች**

**25. የጡረታ መብት**

የጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት እና ምክትል ፕሬዚዳንት ጡረታ የሚያገኙት በጡረታ ህግ መሠረት ይሆናል፡፡

**26. Umo Dandaate Baatooshshe**

1. Xaphoomu yoo mini pirezidantichiranna layinki pirezidantichira umo dandaate baatooshshe baantannihu
   a) Ajanna mitto doorshu diro owaate sbiilloonyunni kairo woy
   b) Bocu doorshu diro ajjinokki yanna owaante ee xissotenni, bisu gawajjonni woy wolqate aliidi wolu korkaatinni biilloonyunni kainoha ikkirooti.
2. Konni quwira cinaanco quwa (1) hunda seerroonni garinni baantanniti umo dandaate baatooshshi umikki doorshu diri owaantera lewu (6) agani xeinsoonnikki damooza ikke mittu doorshu diri alee noo mittu mittunku diri owaantera goofimarchunniha mittu (1) agani xeinsoonniki damooza lende shallanganniha ikkanna lamu doorshu diri alee noo mittu mittunku diri owaantera lamu (2) agani damooza lendanni baantani.
3. Konni quwira cinaancho quwa 2 hunda seerroonni hee'rirono xaphooma baantannihu umo dandaate baatooshshi lemiina shoolu (24) agani damooza roora dinosi.

**27. Biilloonyunni Geegiissate Baatooshshe.**

1. Xaphoomu yoote mini pirezidantichiranna 2ki pirezidantichira biilloonyunni geegiissate baatooshshe baantannihu:-
   a) Ajanna mittu doorshu diro owaante ee biilloonyunni kairo; woy

**26. የመቋቋሚያ አበል**

1. ለጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት እና ምክትል ፕሬዚዳንት የመቋቋሚያ አበል የሚከፈለው፡-
   ሀ) ቢያንስ አንድ የምርጫ ዘመን አገልግሎ ከኃላፊነት ከተነሳ፤ ወይም
   ለ) ከግማሽ የምርጫ ዘመን ያላነሰ ጊዜ አገልግሎ በህመም፣ በአካል ጉዳት ወይም ከአቅም በላይ በሆነ ሌላ ምክንያት ከኃላፊነት የተነሳ እንደሆነ ነው፤
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ሥር በተደነገገው መሠረት የሚከፈለው የመቋቋሚያ አበል ለመጀመሪያው አንድ የምርጫ ዘመን አገልግሎት የስድስት (6) ወር ያልተጣራ ደመወዝ ሆኖ፤ ከአንድ የምርጫ ዘመን በላይ ላለው ለእያንዳንዱ ተጨማሪ የአንድ ዓመት አገልግሎት የመጨረሻው የአንድ (1) ወር ያልተጣራ ደመወዝ እየታከለ የሚሰላ ሲሆን ከሁለት የምርጫ ዘመን በላይ ላለው ለእያንዳንዱ ተጨማሪ የአንድ ዓመት አገልግሎት የሁለት ወር (2) ወር ደመወዝ እየተጨመረ ይከፈላል፤
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 ሥር የተደነገገው ቢኖርም አጠቃላይ የሚከፈለው የመቋቋሚያ አበል ሃያ አራት (24) ወራት ደመወዝ መብለጥ የለበትም፡፡

**27. የኃላፊነት ስንብት ክፍያ**

1. ለጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት እና ምክትል ፕሬዚዳንት የኃላፊነት ስንብት ክፍያ የሚከፈለው፡-
   ሀ) ቢያንስ አንድ የምርጫ ዘመን አገልግሎ ከኃላፊነት ከተነሳ፤ ወይም

b) Boco doorshu diro ajjinokki yanna owaate xissotenni, bisu gawajjonni woy wolqate aleenni ikkinorinni wolu korkaatinni biilloonyunni kainoha ikkirooti.

2. Konni quwira cinaancho quwa (1) hunda seerroonni garinni baantannihu loosu geegoo baatooshshi umikkihu mittu doorshi diri owaantera lewu (6) agani xeinsoonnikki damooza ikke mittu doorshu diri alee noo mittu mittunku diri owaantera goofimarchunniha mittu (1) agani xeinsoonniki damooza lende shallanganniha ikkanna lamu doorshu diri alee noo mittu mittunku diri owaantera lamu (2) agani damooza lendanni baantani.

3. Konni quwira cinaancho quwa (2) hunda seerroonni noo gedee hee’reenna xaphooma baantannihu biilloonyunni geegiissate baatooshshi lemiina shoolu (24) agani damoozinni roora dinosi.

**28. Gallanni Mini Baatooshshenna Gallani Mine**

**1.** Biilloonyunni kaino xaphoomu yoo mini pirezidaantenna 2ki pirezidantichi:-

a) ajanna mittu doorshu diri yanna owaate biilloonyunni kairo woy

b) Bocu doorshu yannanni ajjinokki owaante ee xisssotenni, bisu gawajjonni woy wolqate alee ikkino wolu korkaatinni biilloonyunni kairo gallanni mini baatooshshe baantannisi.

ለ) ከግማሽ የምርጫ ዘመን ያላነሰ ጊዜ አገልግሎ በህመም፣ በአካል ጉዳት ወይም ከአቅም በላይ በሆነ ሌላ ምክንያት ከኃላፊነት ከተነሳ እንደሆነ ነው፤

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ሥር በተደነገገው መሠረት የሚከፈለው የሥራ ስንብት ክፍያ ለመጀመሪያው የአንድ ምርጫ ዘመን አገልግሎት የስድስት (6) ወር ያልተጣራ ደመወዝ ሆኖ ከአንድ የምርጫ ዘመን በላይ ላለው ለእያንዳንዱ ተጨማሪ የአንድ ዓመት አገልግሎት የመጨረሻው የአንድ (1) ወር ያልተጣራ ደመወዝ እየታከለ የሚሰላ ሲሆን ከሁለት ምርጫ ዘመን በላይ ላለው ለእያንዳንዱ ተጨማሪ የአንድ ዓመት አገልግሎት የሁለት ወር (2) ወር ደመወዝ እየተጨመረ ይከፈላል፤

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) ሥር የተደነገገው ቢኖርም የሚከፈለው ጠቅላላ የኃላፊነት ስንብት ክፍያ ከሃያ አራት (24) ወራት ደመወዝ መብለጥ የለበትም፡፡

**28. የመኖሪያ ቤት አበል እና መኖሪያ ቤት28.**

1. ከኃላፊነት የተነሳ የጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት እና ምክትል ፕሬዚዳንት፡-

ሀ) ቢያንስ አንድ የምርጫ ዘመን አገልግሎ ከኃላፊነት ከተነሳ፤ ወይም

ለ) ከግማሽ የምርጫ ዘመን ያላነሰ አገልግሎ በህመም፣ በአካል ጉዳት ወይም ከአቅም በላይ በሆነ ሌላ ምክንያት ከኃላፊነት ከተነሳ የመኖሪያ ቤት አበል ይከፈለዋል፤

2. Konni quwira cinaancho quwa 1 (a) ana (b) hunda seerroonni garinni gallanni mini baatooshshi mitte hinge baantanniha ikke umikki doorshu diri owaantera lewu (6) agani xeinsoonnikki damooza ikke mittu doorshu diri alee noo mittu mittunku diri owaantera mittu (1) agani xeinsoonnikki damooza lende shallanganniha ikkanna lamu doorshu diri alee noo mittu mittunku diri owaantera lamu again (2) damooza lendanni baantanni.

3. Konni quwira cinaancho quwa (2) hunda seerroonnihu heerirono xaphoomma gallanni mini baatooshshi Lemiina Shoolu agani damoozinni roora dinosi.

4. Gallanni minire konni lallawira quwa 8 cinaancho quwa 2 (a) hundaanni seerroonni xaphoomu yoo mini pirezidantichiranna 2ki pirezidantichi aana jeefishshu hee’rannosi.

**29. Kaameelu Baatooshshe**

Xaphoomu yoo mini pirezidantichinna 2ki pirezidantichi:-

1. Ajanna mittu doorshu yanna owaate biilloonyunni kairo woy
2. Bocu doorshu yannanni ajjinokki owaante ee xissotenni, bisu gawjjonni woy wolqate aleenni ikkino wolu korkaatinni biilloonyunni kairo kaameelu baatooshshe baantannisi.
3. Konni quwira cinaancho quwa (1)nna (2) hunda seerroonni garinni kaameelu baatooshshi mitte hinge bantanniha ikke kaimu umikki doorshu diri owaantera lewu (6) agani xeinsoonnikki damooza ikke mittu doorshu diri alee noo mittu

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1(ሀ) እና (ለ) ሥር በተደነገገው መሠረት የመኖሪያ ቤት አበል በአንድ ጊዜ የሚከፈል ሆኖ፤ የመነሻ ክፍያው የስድስት (6) ወር ያልተጣራ ደመወዝ ሆኖ ከአንድ የምርጫ ዘመን በላይ ላለው ለእያንዳንዱ ተጨማሪ የአንድ ዓመት አገልግሎት የአንድ (1) ወር ያልተጣራ ደመወዝ ክፍያ እየታከለ የሚሰላ ሲሆን ከሁለት ምርጫ ዘመን በላይ ላለው ለእያንዳንዱ ተጨማሪ የአንድ ዓመት አገልግሎት የሁለት ወር (2) ወር ደመወዝ እየተጨመረ ይከፈላል፤

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) ሥር የተደነገገው ቢኖርም አጠቃላይ የመኖሪያ ቤት አበል ክፍያ ሃያ አራት (24) ወራት ደመወዝ መብለጥ የለበትም፤

4. ስለ መኖሪያ ቤት በዚህ አዋጅ አንቀጽ 8 ንኡስ አንቀጽ 2 (ሀ) ሥር የተደነገገው ለጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዝዳንት እና ምክትል ፕሬዚዳንት ላይ ተፈጻሚነት ይኖረዋል::

**29. የተሸከርካሪ አበል**

የጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት እና ምክትል ፕሬዚዳንት፡-

1. ቢያንስ አንድ የምርጫ ዘመን አገልግሎ ከኃላፊነት ከተነሳ፤ ወይም
2. ከግማሽ የምርጫዘመን ያላነሰ አገልግሎ በህመም፣ በአካል ጉዳት ወይም ከአቅም በላይ በሆነ ሌላ ምክንያት ከኃላፊነት ከተነሳ የተሸከርካሪ አበል ይከፈለዋል፤
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እና (2) ሥር በተደነገገው መሠረት የተሸከርካሪ አበል በአንድ ጊዜ የሚከፈል ሆኖ የመነሻ ክፍያው የስድስት (6) ወራት ሙሉ ደመወዝ ሆኖ ከአንድ የምርጫ

mittunku diri owaantera mittu (1) againi xeinsoonnikki damooza lende shallanganniha ikkanna lamu doorshu diri alee noo mittu mittunku diri owaantera lamu agani (2) damooza lendanni baantanni.

4. Konni quwira cinaancho quwa (1) nna (2) hunda seerroonniri heerirono baantannihu kaameelu baatooshshi xaphooma Lemiina Shoolu (24) agani damooza roora dinosi.

5. Lame doorshu yannanna hakkuy ali owaante uyno xaphoomu yoo mini pirezidantichira hattee yannara roore biirote sooreeyye horonsidhanno gedee kaameela qoqqowu mootimma baajeetenni hirre uynannisi.

6. Konni quwira cinaancho quwa 5 garinni kaameela hirre uynanni xaphoomu yoo mini pirezidantichira kaameelu baatooshshe afi'rate qoosso diheedhannosi.

**31. Meessi Hobbaate Agarooshshi Owaante**

1. Xaphoomu yoo mini pirezidantichinna 2^ki^ pirezidantichi biilloonyu aana noo yannara meessi hobbaate agarooshshe assinannansa heedhinoha ikkiro biilloonyunni ka''anno yannarano agarooshshe assinanninsa.

2. Agarooshshu daninna bikki gumulamannohu agarooshshe assiissanno bissanni ikkanno.

**32. Owaantete Taje Woraqata**

1. Billoonyunni kaino xaphoomu yoo mini pirezidantichinna 2^ki^ pirezidantichi:-

ዘመን በላይ ላለው ለእያንዳንዱ ተጨማሪ የአንድ አመት አገልግሎት የአንድ (1) ወር ክፍያ እየታከለ የሚሰላ ሲሆን ከሁለት ምርጫ ዘመን በላይ ላለው ለእያንዳንዱ ተጨማሪ አገልግሎት የሁለት ወር (2) ወር ደመወዝ እየተጨመረ ይከፈላል፤

4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እና (2) ሥር የተደነገገው ቢኖርም ለተሸከርካሪ አበል የሚከፈለው አጠቃላይ ክፍያ ሃያ አራት (24) ወራት ደመወዝ መብለጥ የለበትም፡፡

5. ሁለት የምርጫ ዘመንና ከዚያ በላይ ላገለገለ ለጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚደንት በወቅቱ አብዘኛዎቹ የቢሮ ኃላፊዎች የሚጠቀሙበት ተሽከሪካሪ ዓይነት በክልሉ መንግሥት በጀት ተገዝቶ ይሰጣል፡፡

6. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 5 መሠረት መኪና ተገዝቶ የሚሰጠዉ የጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚደንት የተሸከርካሪ አበል የማግኘት መብት አይኖረዉም፡፡

**31. የግል ደህንነት ጥበቃ አገልግሎት**

1. የጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት እና ምክትል ፕሬዚዳንት በኃላፊነት ላይ በነበሩበት ወቅት የግል ደህንነት ጥበቃ ይደረግላቸው የነበረ እንደሆነ ከኃላፊነት ላይ ሲነሱም ጥበቃ ይደረግላቸዋል፤

2. የጥበቃ ኃይሉ ዓይነትና መጠን ጥበቃውን በሚያካሄደው አካል የሚወሰን ይሆናል፡፡

**32. የአገልግሎት ምስክር ወረቀት**

1. ከኃላፊነት የተነሳ የጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት እና ምክትል ፕሬዚዳንት፡-

a) Lame doorshu yanna woy hakkiinni sae owaante uynoha ikkiro umi deerri owaantete taje woraqata uynannisi.

b) Mittu doorshu yanna aleenninna lamu doorshi yanna woroonni owaante uynoha ikkiro layinki deerri owaantete taje woraqata uynannisi.

c) Mitto wo’ma doorshu yanna owaante uynoha ikkiro sayikki deerri owaantete taje woraqata uynannisi.

d) Bocu doorshu yanna aleenni mitte doorshu yanna woroonni owaante uyimoha ikkiro shoolki deerri owaantete taje woraqata uynannisi.

2. Uynannihu owaantete taje woraqati Amaalete Mini songaafichinni malaatisamannoha ikkanno.

3. Ayno owaantete taje woraqata uynoonnihu:-

a) Mootimmate fayyimmate uurrinsha giddo uynanni fayyimmate owaante balaxotenni afi’ranno;

b) Dagate gambooshshira ayirrinyu base uynannisi.

4. Umi deerri owaantete taje woraqta uynoonnisihu konni quwi cinaancho (3) hunda seerrooonni qoossonna horo gobbaanni ledeno haja la’anno bisi ledo amaalamatenni:-

a) Diplomatikete pasipoorte uynannisi gede assinanni;

b) Horophillu fooliishshiranno basera baxxinoha ayirrinyu owaante /VIP/ afi’ranno gede assinanni;

ሀ) ሁለት የምርጫ ዘመን እና ከዚያ በላይ ያገለገለ ከሆነ አንደኛ ደረጃ የአገልግሎት የምስክር ወረቀት ይሰጠዋል፤

ለ) ከአንድ የምርጫ ዘመን በላይ እና ከሁለት የምርጫ ዘመን በታች ያገለገለ ከሆነ ሁለተኛ ደረጃ የአገልግሎት የምስክር ወረቀት ይሰጠዋል፤

ሐ) አንድ የምርጫ ዘመን ያገለገለ ከሆነ ሶስተኛ ደረጃ የአገልግሎት የምስክር ወረቀት ይሰጠዋል፤

መ) ከግማሽ የምርጫ ዘመን በላይ እና ከአንድ የምርጫ ዘመን በታች ያገለገለ ከሆነ አራተኛ ደረጃ የአገልግሎት የምስክር ወረቀት ይሰጠዋል፤

2. የሚሰጠው የአገልግሎት የምስክር ወረቀት በምክር ቤቱ አፈ-ጉባኤ የሚፈረም ይሆናል፤

3. ማንኛውም የአገልግሎት የምስክር ወረቀት የተሰጠው ባለመብት:-

ሀ) በመንግሥት የጤና ተቋም ውስጥ የሚሰጠውን የህክምና አገልግሎት ቅድሚያ ያገኛል፤

ለ) በህዝባዊ ስብሰባዎች ላይ የክብር ቦታ ይሰጠዋል፤

4 አንደኛ ደረጃ የአገልግሎት የምስክር ወረቀት የተሰጠው ባለመብት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) ሥር ከተደነገጉት መብት እና ጥቅሞች በተጨማሪ ጉዳዩ ከሚመለከተው አካል ጋር በመመካከር:-

ሀ) ዲፕሎማቲክ ፓስፖርት እንዲሰጠው ይደረጋል፤

ለ) በአውሮፕላን ማረፊያ ልዩ የክብር አገልግሎት (VIP) እንዲያገኝ ይደረጋል፤

c) Horophillunni gobbate giddo harinsho assinanni woyte ha'nanni tikkeette 50% anga mootimma baatannoha ikkanno.

5. Layinki deerri owaantete woraqata uynoonnisi horaameessi konni quwira cinaancho kiro (3) hunda gumulloonni qoossonna horo gobbaanni noo hajo la'annonsa bissa ledo amaalamatenni;--

a) Diplomatikete pasiporte uynanisi gede assinanni;

b) Horophillu dirrannowa baxxino ayirrinyi owaante (VIP) afi'ranno gede assinanni;

c) Horophillunni gobbate giddo ha'rinshora kaa'litanno tikkeette baatooshshe 25% mootimma baattanno gede assinanni.

6. Sayikki deerri owaantete taje woraqata uynoonnisi qoossaanchi konni quwira cinaancho quwa (3) hunda seerroonni qoossonna horo goobbaanni noo horo hajo la'anno bisi ledo amaalamatenni;-

a) Diplomatikete paasiporte uynannisi gede assinanni;

b) Horophillu fooliishshi'ranno basera baxxinoha ayirrinyu owaantte /VIP/ afi'ranno gede assinanni;

c) Horophilunni gobbate giddo assinanni ha'rinshora tikkeetete baatooshshe 10% mootimma baatannoha ikkanno.

7. Shoolki deerriha owaantete taje woraqata uynoonnisihu konni quwira cinaancho quwa (3)

ሐ) በአየር የአገር ውስጥ በረራ ሲያደርግ የአየር ቲኬቱ ዋጋ ሃምሳ በመቶ (50%) በመንግሥት የሚሸፈን ይሆናል፤

5. ሁለተኛ ደረጃ የአገልግሎት የምስክር ወረቀት የተሰጠው ባለመብት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 ሥር ከተደነገጉት መብት እና ጥቅሞች በተጨማሪ ጉዳዩ ከሚመለከተው አካል ጋር በመመካከር፦

ሀ) ዲፕሎማቲክ ፓስፖርት እንዲሰጠው ይደረጋል፤

ለ) በአውሮፕላን ማረፊያ ልዩ የክብር አገልግሎት (VIP) እንዲያገኝ ይደረጋል፤

ሐ) በአየር የአገር ውስጥ በረራ ሲያደርግ የአየር ቲኬቱ ዋጋ ሃያ አምስት በመቶ (25%) በመንግሥት የሚሸፈን ይሆናል፤

6. ሶስተኛ ደረጃ የአገልግሎት የምስክር ወረቀት የተሰጠው ባለመብት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 ሥር ከተደነገጉት መብት እና ጥቅሞች በተጨማሪ ጉዳዩ ከሚመለከተው አካል ጋር በመመካከር፦

ሀ) ዲፕሎማቲክ ፓስፖርት እንዲሰጠው ይደረጋል፤

ለ) በአውሮፕላን ማረፊያ ልዩ የክብር አገልግሎት (VIP) እንዲያገኝ ይደረጋል፤

ሐ) በአየር የአገር ውስጥ በረራ ሲያደርግ የአየር ቲኬቱ ዋጋ አስር በመቶ (10%) በመንግሥት የሚሸፈን ይሆናል፤

7. አራተኛ ደረጃ የአገልግሎት የምስክር ወረቀት የተሰጠው ባለመብት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 ሥር ከተደነገጉት መብት እና ጥቅሞች በተጨማሪ

hunda seerroonni qoossonna horo gobbaanni hajo la'annosi bisi ledo amaalamatenni;-

a) Diplomaatikete paasiporte uynannisi gede assinanni;

b) Horophillu fooliishshiranno basera baxxinoha ayirrinyu owaante /VIP/ afi'rano gede assinanni.

**33. Loosu Gaamooshshe**

1. Yooaanchimmatenni kainoha xaphoomu yoo mini pirezidantichi woy 2[ki] pirezidantichi yooaanchimmate higara xa'miriro woy wole basera gaamamara hasatto noosiha ikkiro seeru ogimma madawera gaamamanno gede assinanni.

2. Konni quwira cinaancho quwa (1) hunda seerroonnihu noo gedee he'reenna loosu gaamo uynoonnisi pirezidantichi woy 2[ki] pirezidantichi konni lallawira seerroonni qoosssonna horo afi'rate qoosso diheedhannosi.

**34. Tenne Kalqenni Rewootenni Baxxitino Qoossaano Qoossonna Horo**

**1**. Xaphoomu yoo mini pirezidantichi woy 2[ki] pirezidantichi loosu aana hee're tenne kalqennii rewootenni baxxiro;-

a) Rewoosi ledo xaadinorinni fultino fulo baatate (3) agana rorinokki xeinsoonnikki damooza maatesira baantanni;

b) Biilloonyunni kainoha ikkoommero baantasira hasiisanno umo dandaate

ጉዳዩ ከሚመለከተው አካል ጋር በመመካከር፡-

ሀ) ዲፕሎማቲክ ፓስፖርት እንዲሰጠው ይደረጋል፤

ለ) በአውሮፕላን ማረፊያ ልዩ የክብር አገልግሎት (VIP) እንዲያገኝ ይደረጋል፡፡

**33. የሥራ ምደባ**

1. ከኃላፊነት የተነሳ የጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት ወይም ምክትል ፕሬዚዳንት ወደ ዳኝነት ሥራ ለመመለስ ከጠየቀ ወይም ሌላ ቦታ ለመመደብ ፍላጎት ያለው ከሆነ ባለው ህግ ላይ በመመሥረት እንዲመደብ ይደረጋል፤

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ሥር የተደነገገው ቢኖርም የሥራ ምደባ የተሰጠው ፕሬዚዳንት ወይም ምክትል ፕሬዚዳንት በዚህ አዋጅ የተደነገጉትን መብት እና ጥቅሞች ለማግኘት መብት የለውም፡፡

**34. ከዚህ ዓለም በሞት ስለተለየ ባለመብት መብት እና ጥቅሞች**

1. የጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት ወይም ምክትል ፕሬዚዳንት በሥራ ላይ እያለ ከዚህ ዓለም ላይ በሞት ቢለይ፡-

ሀ) ከሞቱ ጋር ተያይዞ የወጣውን ወጪ ለመሸፈን የሶስት (3) ወር ያልተጣራ ደመወዝ ለቤተሰቦቹ ይከፈላል፤

ለ) ከኃላፊነት ቢነሳ ኖሮ ሊከፈለው ይገባ የነበረው መልሶ የመቋቋሚያ አበል፣ የኃላፊነት ስንብት ክፍያ፤ የመኖሪያ ቤት

baatooshshe, loosu geegoo baatooshshe, gallani mini baatooshshenna kaameelu baatooshshe maatesira baantanni.

2. Qoossanchu afi'ra hasiissannosi horo afi'rate albaanni tenne kalqenni rewootenni baxxiro baantanni hee'noonnisi umo dandaate baatooshshe, biilloonyunni geegiissate baatooshshe, gallanni mini baatooshshenna hodhishshu baatooshshe maatesira baantanni;

3. Qoossaanchu loosu aana he'ree woy biilloonyunni kae tenne kalqenni rewootenni baxxiro;-

a) Rewoote duduwonna heeshshote dhagge mootimmate tuqu xaadooshshinni dudunbanni;

b) Madaarshu amanyoote qoqqowu maarshi baandenninna ayirrinyu dukkisaanonni jeefinsanni;

c) Qoqqowu mootmma aliidi biilto madaarshu amanyoote jeefinsanni yannara basete leelte daraarchu gungune worate amanyoote assitanno;

d) Madaarshu amanyooti madaarshu jeefissannorinni jeefamannoha ikkanna tenne hajora hasiissanno fulo mootimma baattanno.

አበል እና የተሽከርካሪ አበል ለቤተሰቡ ይከፈላል፤

2. ባለመብቱ ጥቅሞችን ከማግኘቱ በፊት ከዚህ ዓለም በሞት ቢለይ ሊከፈለው ይገባ የነበረው የመቋቋሚያ አበል፤ የኃላፊነት ስንብት ክፍያ፤ የመኖሪያ ቤት አበል እና የተሽከርካሪ አበል ለቤተሰቡ ይከፈላል፤

3. ባለመብቱ በሥራ ላይ እያለ ወይም ከኃላፊነት ተነስቶ ከዚህ ዓለም በሞት ቢለይ፡-

ሀ) ዜና እረፍቱ እና የህይወት ታሪኩ በመንግሥት ሚዲያ ይነገራል፤

ለ) የቀብር ሥነ-ሥርዓቱ የክልሉ ማርሽ ባንድና የክብር ዘብ በተገኘበት ይፈጸማል፤

ሐ) የክልሉ ከፍተኛ የመንግሥት ባለሥልጣን በቀብር ሥነ-ሥርዓቱ ላይ በመገኘት የአበባ ጉንጉን የማስቀመጥ ሥነ- ሥርዓት ይፈጽማል፤

መ) የቀብር ሥነ-ሥርዓቱ በቀብር አስፈጻሚዎች የሚፈጸም ሆኖ ለዚህ የሚወጣው ወጪ በመንግሥት የሚሸፈን ይሆናል፤

## Cinaancho Gafa Lame

### Xaphoomu Yoo mini Yooaano, Aliidi Yoo Mini Pirezidntichnna Aliidi Yoo Mini $2^{ki}$ Pirezidantichi Qoossonna Horo

**35. Biilloonyunni Ka'ino Xaphoomu Yoo Mini Yooaanonna Aliidi Yoo Mini Pirezidantooti**

Biilloonyunni ka'inori xaphoomu yoo mini yooaano, aliidi yoo mini pirezidantichi, aliidi yoo mini $2^{ki}$ pirezidantichi wommete baatooshshe afidhannohu wommete seeri garinni ikkanno.

**36. Umo Dandaate Baatooshshe**

1. Xaphoomu yoo mini yooaanchi, aliidi yoo mini pirezidantichinna aliidi yoo mini $2^{ki}$ pirezidantichi:-

   a) Ajanna lame doorshu diro owaante ee biilloonyunni kairo; woy

   b) Mitto doorshu dirinni ajjinokki owaante ee xissotenni, bisu gawajjonni woy wolqate aleenni ikkino wolu korkaatinni biilloonyunni kairo umo dandaate baatooshshe baantannisi**.**

2. Konni quwira cinancho quwa (1) hunda seerroonni garinni umo dandaate baatooshshi umikki doorshu diri owaantera lamu (2) agani xeinsoonnikki damooza ikke lamu doorshu diri ale noo mittu mittunku diri owaantera mittunni shoolki anga (1/4) aganunniha xeinsoonnikki damooza lende shallanganniha ikkanno.

## ንኡስ ክፍል ሁለት

### የጠቅላይ ፍርድ ቤት ዳኞች ፣ የከፍተኛ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት እና ምክትል ፕሬዚዳንት መብትና ጥቅሞች

**35. ከኃላፊነት የተነሱ የጠቅላይ ፍርድ ቤት ዳኞችና የከፍተኛ ፍርድ ቤት ፕሬዝዳንቶች**

ከኃላፊነት የተነሱ የጠቅላይ ፍርድ ቤት ዳኞች፣ የከፍተኛ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት፣ ምክትል ፕሬዚዳንት ጡረታ የሚያገኙት በጡረታ ህግ መሠረት ይሆናል፤

**36. የመቋቋሚያ አበል**

1. የጠቅላይ ፍርድ ቤት ዳኛ፣ የከፍተኛ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንትና የከፍተኛ ፍርድ ቤት ምክትል ፕሬዚዳንት፡-

   ሀ) ቢያንስ ሁለት የምርጫ ዘመን አገልግሎ ከኃላፊነት ከተነሳ፤ ወይም

   ለ) አንድ የምርጫ ዘመን ያላነሰ አገልግሎ በህመም፣ በአካል ጉዳት ወይም ከአቅም በላይ በሆነ ሌላ ምክንያት ከኃላፊነት ከተነሳ የመቋቋሚያ አበል ይከፈለዋል፤

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ሥር በተደነገገው መሠረት የሚከፈለው የመቋቋሚያ አበል ለመጀመሪያው ሁለት የምርጫ ዘመን አገልግሎት የሁለት (2) ወር ያልተጣራ ደመወዝ ሆኖ ከሁለት የምርጫ ዘመን በላይ ላለው ለእያንዳንዱ ተጨማሪ የአንድ ዓመት አገልግሎት የመጨረሻው አንድ አራተኛ (1/4) የወር ያልተጣራ

3 Konni quwira cinaancho quwa (2) hunda seerroonnihu hee’rirono xaphoomu umo dandaate baatooshshi tonaa ontu (15) agani damooza roora dinosi.

**37. Biilloonyunni Geegiissate Baatooshshe**

1. Biilloonyuunni kainohu xaphoomu yoo mini yooaanchira, aliidi yoo mini pirezidantichiranna aliidi yoo mini 2ki pirezidantichira biiloonyunni geegiissate baatooshshe baantanninsa.
2. Konni quwira cinaancho quwa (1) hunda seerroonni garinni biilloonyunni geegiissate baatooshshi umikki lamu doorshu diri owaantera lamu (2) agani xeinsoonnikki damooza ikkeenna lamu doorshu diri ale noo mittu mittunku diri owaantera mittunni shoolki anga (1/4) aganunniha xeinsoonnikki damooza lende shallanganniha ikkanno.
3. Konni quwira cinaancho quwa (2) hunda seerroonniri hee’rirono xaphoomu biilloonyunni geegiissate baatooshshi tonna onte (15) agani damoozinni roora dinosi.

**38. Gallanni Mini Baatooshshenna Gallanni Mine**

1. Xaphoomu yoo mini yooaanchi, aliidi yoo mini pirezidantichinna aliidi yoo mini 2ki pirezidantichi:-

   a) Ajanna lame doorshu diro owaate

ደመወዝ እየታከለ የሚሰላ ይሆናል፡፡

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) ሥር የተደነገገው ቢኖርም የሚከፈለው አጠቃላይ የመቋቋሚያ አበል ክፍያ ከአስራ አምስት (15) ወራት ደመወዝ መብለጥ የለበትም፡፡

**37. የኃላፊነት ስንብት ክፍያ**

1. ከኃላፊነት የተነሳ የጠቅላይ ፍርድ ቤት ዳኛ፣ የከፍተኛ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት እና የከፍተኛ ፍርድ ቤት ምክትል ፕሬዚዳንት የኃላፊነት ስንብት ክፍያ ይከፈለዋል፤
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ሥር በተደነገገው መሠረት የኃላፊነት ስንብት ክፍያ የሚከፈለው ለመጀመሪያው ሁለት የምርጫ ዘመን አገልግሎት የሁለት (2) ወር ያልተጣራ ደመወዝ ሆኖ ከሁለት የምርጫ ዘመን በላይ ላለው ለእያንዳንዱ ተጨማሪ የአንድ ዓመት አገልግሎት የመጨረሻው አንድ አራተኛ (1/4) የወር ያልተጣራ ደመወዝ እየታከለ የሚሰላ ይሆናል፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) ሥር የተደነገገው ቢኖርም የሚከፈለው አጠቃላይ የኃላፊነት ስንብት ክፍያ ከአስራ አምስት (15) ወራት ደመወዝ መብለጥ የለበትም፡፡

**38. የመኖሪያ ቤት አበል እና የመኖሪያ ቤት**

1. የጠቅላይ ፍርድ ቤት ዳኛ፣ የከፍተኛ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት እና የከፍተኛ ፍርድ ቤት ምክትል ፕሬዚዳንት፡-

   ሀ) ቢያንስ ሁለት የምርጫ ዘመን አገልግሎ

biillloonyunni kairo; woy

b) Mitto doorshu diro ajjinokki yanna owaate xissotenni, bisu gawajjonni woy wolqate aleeni ikkino wolu korkaatinni biilloonyunni kairo gallani mini baatooshshe baantannisi.

2. Konni quwira cinaancho quwa (1) garinni xaphoomu yoo mini yooaanchira, aliidi yoo mini pirezidantichiranna aliidi yoo mini 2ki pirezidantichira gallanni mini baatooshshe mitte hinge baantanniha ikke, kaimu lamu (2) agani xeinsoonnikki damoozi baatooshshe ikkeenna lamu doorshu diri ale noo mittu mittunku diri owaantera mittunni shoolki anga (1/4) aganunniha xeinsoonnikki damooza lende shallanganniha ikkanno.

3. Konni quwira cinaancho quwa (2) hunda seerroonniri hee'rirono xaphooma gallanni mini baatooshshi tonaa onte (15) agani damooza roora dinosi.

**39. Kaameelu Baatooshshe**

1. Xaphoomu yoo mini yooaanchi, aliidi yoo mini pirezidantichinna aliidi yoo mini 2ki pirezidantichi:-

a) ajanna lamu doorshu diro owaate biilloonyunni kairo; woy

b) Boco doorshu diro ajjinokki owaante ee xissotenni, bisu gawajjonni, wolqate aleenni ikkino wolu korkaatinni biilloonyunni kairo kaameelu baatooshshe baantannisi.

ከኃላፊነት ከተነሳ፤ ወይም

ለ) ከአንድ የምርጫ ዘመን ያላነሰ አገልግሎ በህመም፣ በአካል ጉዳት ወይም ከአቅም በላይ በሆነ ሌላ ምክንያት ከኃላፊነት ከተነሳ የመኖሪያ ቤት አበል ይከፈለዋል፤

2 በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ለጠቅላይ ፍርድ ቤት ዳኛ፣ የከፍተኛ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት እና የከፍተኛ ፍርድ ቤት ምክትል ፕሬዚዳንት የመኖሪያ ቤት አበል በአንድ ጊዜ የሚከፈል ሆኖ መነሻው የሁለት (2) ወር ያልተጣራ ደመወዝ ክፍያ ሆኖ ከሁለት የምርጫ ዘመን በላይ ላለው ለእያንዳንዱ ተጨማሪ የአንድ ዓመት አገልግሎት የአንድ አራተኛ (1/4) የወር ያልተጣራ ደመወዝ እየታከለ የሚሰላ ይሆናል፡፡

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) ሥር የተደነገገው ቢኖርም አጠቃላይ ለመኖሪያ ቤት የሚከፈለው አበል ከአስራ አምስት (15) ወር ደመወዝ መብለጥ የለበትም፤

**39. የተሸከርካሪ አበል**

1. የጠቅላይ ፍርድ ቤት ዳኛ፣ የከፍተኛ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንትና የከፍተኛ ፍርድ ቤት ምክትል ፕሬዚዳንት፡-

ሀ) ቢያንስ ሁለት የምርጫ ዘመን አገልግሎ ከኃላፊነት ከተነሳ፤ ወይም

ለ) ከአንድ ያላነሰ የምርጫ ዘመን አገልግሎ በህመም፣ በአካል ጉዳት ወይም ከአቅም በላይ በሆነ ሌላ ምክንያት ከኃላፊነት ከተነሳ የተሽከርካሪ አበል ይከፈለዋል፤

2. Konni quwira cinaancho quwa (1) hunda xaphoomu yoo mini yooaanchi, aliidi yoo mini pirezidantichira, aliidi yoo mini 2ki pirezidantichira kaameelu baatooshshe mitte hinge baantanniha ikke kaimu baatooshshi lamu (2) agani xeinsoonnikki damooza ikke mittu doorshu diri ale noo mittu mittunku diri owaantera mittunni shoolki anga (1/4) aganunniha xeinsoonnikki damooza lende shallanganniha ikkanno.
3. Konni quwira cinaancho quwa (2) hunda seerroonniri he'rirono xaphooma kaameelu baatooshshi tonaa onte (15) agani damoozinni roora dinosi.

**40.Tenne Kalqenni Rewootenni Baxxino Qoossaanchi Qoossonna Horo**

1. Xaphoomu yoo mini yooaanchi, aliidi yoo mini pirezidantichi, aliidi yoo mini 2ki pirezidantichi loosu aana hee're rewooteni baxxiro;-

   a) Rewoote ledo xaaddino fulora hasiisannoha sasu (3) agani xeinsoonnikki damooza maatesira baantanni.

   b) Biilloonyuunni kainoha ikkiro baantara hasiisannoha umo dandaate baatooshshe, biilloonyunni geegiissate baatooshshe, gallani mini baatooshshenna kaameelu baatooshshe maatesira baantanni.

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ለጠቅላይ ፍርድ ቤት ዳኛ፣ የከፍተኛ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት፣ የከፍተኛ ፍርድ ቤት ምክትል ፕሬዚዳንት የተሸከርካሪ አበል በአንድ ጊዜ የሚከፈል ሆኖ የመነሻ ክፍያው የሁለት (2) ወር ያልተጣራ የደመወዝ ክፍያ ሆኖ፤ ከሁለት የምርጫ ዘመን በላይ ላለው ለእያንዳንዱ ተጨማሪ የአንድ ዓመት አገልግሎት አንድ አራተኛ (1/4) ወር ደመወዝ እየታከለ የሚሰላ ይሆናል፡፡

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 ሥር የተደነገገው ቢኖርም አጠቃላይ የተሸከርካሪ አበል ክፍያ ከአስራ አምስት (15) ወራት ደመወዝ መብለጥ የለበትም፡፡

**40. ከዚህ ዓለም በሞት ስለተለየ ባለመብት መብት እና ጥቅሞች**

1. የ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ዳኛ፣ የከፍተኛ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት፣ የከፍተኛ ፍርድ ቤት ምክትል ፕሬዚዳንት በሥራ ላይ እያለ ከዚህ ዓለም ላይ በሞት ቢለይ፡-

   ሀ) ከሞቱ ጋር ተያይዞ የወጣውን ወጪ ለመሸፈን የሶስት (3) ወር ያልተጣራ ደመወዝ ለቤተሰቦቹ ይከፈላል፤

   ለ) ከኃላፊነት ተነስቶ ቢሆን ኖሮ ሊከፈለው ይገባ የነበረው የመቋቋሚያ አበል፣ የኃላፊነት ስንብት ክፍያ፤ የመኖሪያ ቤት አበል እና የተሸከርካሪ አበል ለቤተሰቡ ይከፈላል፤

## Gafa Onte

## Gutu Wodhi Woro

### Biilloonyimmatenna Dooramate Soqqansho Diro

**41. Owaantete Diri Kiironna Qoossote Xaadoshshe**

1. Qoqqowu pirezidantichi, layinki prezidantichi, biirote sooreessi, komishiinere, qaru dayrekiterichi, layinki biirote sooreessi, zoonete qaru gashshaanchi, zoonete layinki gashshaanchi, rejiopolitanete quchumi kantiiwi, rejiopolitanete quchumi layinki kantiiwi, qoqqowu Amaale Mini songaafichi, layinki songaafichi, uurrinshu komite ganbisaanchi, uurrinshu komite laayinki ganbisaanchi, borrote mini sooreessi, rejiopolitanete quchumi songaafichinna layinki songaafichi woy konni deerrinni mootoo'mitino biilto uytino rosichi owaante konni lallawi garinni hedote giddora eessine la'nannita ikkitanno.

2. Qoqqowu pirezidantichi, layinki prezidantichi, biirote sooreessi, komishiinere, qaru dayrekiterichi, layinki biirote sooreessi, zoonete qaru gashshaanchi, zoonete layinki gashshaanchi, rejiopolitanete quchumi kantiiwi, rejiopolitanete quchumi layinki kantiiwi, qoqqowu Amaale Mini songaafichi, layinki songaafichi, uurrinshu komite ganbisaanchi, uurrinshu komite layinki ganbisaanchi, borrote mini sooreessi, rejiopolitanete quchumi songaafichinna layinki

## ክፍል አምስት

## የወል ድንጋጌዎች

### የተሿሚነት እና የተመራጭነት የአገልግሎት ዘመን

**41. የአገልግሎት ዘመን አቆጣጠር እና የመብት ግንኙነት**

1. የክልሉ ፕሬዚዳንት፣ ምክትል ፕሬዚዳንት፣ የቢሮ ኃላፊ፣ ኮሚሽነር፣ ዋና ዳይሬክተር፣ ምክትል የቢሮ ኃላፊ፣ የዞን ዋና አስተዳዳሪ፣ የዞን ምክትል አስተዳዳሪ፣ የሬጂኦፖሊታን ከተማ ከንቲባ፣ ምክትል ከንቲባ፣ የክልሉ ምክር ቤቱ አፈ- ጉባኤ፣ ምክትል አፈ-ጉባኤ፣ ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ፣ የጽህፈት ቤት ኃላፊ፣ ቋሚ ኮሚቴ ምክትል ሰብሳቢ፣ የሬጂኦፖሊታን ከተማ አፈ-ጉባኤ እና ምክትል አፈ-ጉባኤ ወይም በተመሳሳይ ደረጃ ያለ ተሿሚ የሰጠው አገልግሎት በዚህ አዋጅ መሠረት በሚያዝለት አገልግሎት ውስጥ ይታሰብለታል፤

2. የክልሉ ፕሬዚዳንት፣ ምክትል ፕሬዚዳንት፣ የቢሮ ኃላፊ፣ ኮሚሽነር፣ ዋና ዳይሬክተር፣ ምክትል የቢሮ ኃላፊ፣ የዞን ዋና አስተዳዳሪ፣ የዞን ምክትል አስተዳዳሪ፣ የሬጂኦፖሊታን ከተማ ከንቲባ፣ ምክትል ከንቲባ፣ የክልሉ ምክር ቤቱ አፈ- ጉባኤ፣ ምክትል አፈ-ጉባኤ፣ ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ፣ የጽህፈት ቤት ኃላፊ፣ ቋሚ ኮሚቴ ምክትል ሰብሳቢ፣ የሬጂኦፖሊታን ከተማ አፈ-ጉባኤ እና ምክትል አፈ-ጉባኤ ወይም በተመሳሳይ ደረጃ ላይ

songaafichi woy konni deerrinni mootoo’mitino biili dooramara woy mootoo’mara albaanni uyno owaante konni lallawi garinni loosu rosicho assine amandannisi.

3. Konni quwira cinaancho quwa 1-2 hunda seerroonni garinni balanxe xawinsoonni owaante konni lallawinni woy la’’annosi federaalete seeri garinni qoossaanchoho balaxe qoossosinna horosi afisiisinoha ikkiro konni lallawi garinni amandannisi owaante diheedhanno.

4. Mitte hige Amaalete Mini miilanna albiidi mootimmate sooreessa ikkinohu afi’ranno qoossonna horo mereerinni roortannota afi’ranno.

5. Babbaxxino biilloonyi deerrinni gaamame owaatanni noo qoossaanchi hiitte yannarano gaamame noo deerrira konni lallawi garinni uynannisi qoossonna horo agarantannosi.

**42. Qoossona Horo Loosu Aana Hossanno Yanna**

Biilloonyunni kaino qoosaanchi kunni lallawinni seerroonni qoossonna horo xa’mi’ri barrinni hanafe sasu agani giddo baatooshshe afi’rannoha ikke wolqate aleenni ikkanno qarri kalaqamiro kayinni mittu diri geeshsha qoossaanchu umisi woy lekkisaanchunni baatooshshe xa’mi’rate qoosso heedhannosi.

የሚገኝ የመንግሥት ተሿሚ ከመመረጡ ወይም ከመሾሙ በፊት የሰጠው አገልግሎት በዚህ አዋጅ መሠረት በሚያዝለት የሥራ ልምድ ላይ ይታሰብለታል፤

3. በዚህ አንቀጽ ከንዑስ አንቀጽ 1-2 ሥር በተደነገገው መሠረት ቀድሞ የተገለጸው አገልግሎት በዚ ህ

አዋጅ ወይም በሚመለከተው የፌዴራል ህግ መሠረት ለባለመብቱ ቀድሞ መብት እና ጥቅሞች ያስገኘለት ከሆነ በዚህ አዋጅ መሠረት የሚያዝለት አገልግሎት አይኖርም፤

4. በአንድ ጊዜ የምክር ቤቱ አባል እና ከፍተኛ የመንግሥት ኃላፊ የነበረ ባለመብት ከሚያገኛቸው መብት እና ጥቅሞች መካከል የሚበልጠውን ያገኛል፤

5. በተለያየ የኃላፊነት ደረጃዎች ላይ ተመድቦ እያገለገለ የነበረ ባለመብት በማናቸውም ጊዜ ተመድቦበት በነበረው የኃላፊነት ደረጃ በዚህ አዋጅ መሠረት የሚሰጠው መብት እና ጥቅሞች ይጠበቅለታል።

**42. መብትና ጥቅሞች መተግበሪያ ጊዜ**

ከኃላፊነት የተነሣው ባለመብት በዚህ አዋጅ የተደነገጉ መብትና ጥቅሞችን ከጠየቀበት ቀን ጀምሮ ባሉት በሦስት ወራት ጊዜ ውስጥ ክፊያዉን የሚያገኝ ሆኖ ከአቅም በላይ የሆነ ችግር ካጋጠመዉ ግን እስከ አንድ ዓመት ድረስ ባለመብቱ ወይም ተወካዩ ክፍያውን የመጠየቅ መብት ይኖረዋል።

**43. Qoossonna Horo Afi'ra Hooltanno Ikkitubba.**

1. Hiikkuno pirezidantichu, layinki pirezidantichi, biirote sooreessi, komishiinere, qara dayrektere, layinki biirote sooreessi, rejiopolitanete quchumi kantiibi, layinki kantiibi, zoonete qaru gashshaanchi, layinki lashshaanchi woy togoo deerrira mootoonsinoonnihu;-

   a) Umisi fajjonni biilloonye aguriro; woy

   b) Mussinnu jaddo looseenna yoote mine hunaancho ikkinota buunxoonniha ikkiro konni lallawira worroonni qoossonna horo diafi'ranno.

2. Ayno Amaalete Mini songaafichi, Amaalete Mini layinki songaafichi, uurrinshu komite ganbisaanchi, uurrinshu komite layinki ganbisaanchi, borrote mini sooreessi, rejiopolitanete quchumi songaafichi, rejiopolitanete quchumi layinki songaafichi woy konni deerrira mootoo'mitinorinna Amaalete Mini miilla;-

   a) Umisi fajjonni biilloonye aguriro; woy

   b) Mussinnu jaddo looseenna yoote mine hunaancho ikkinota buunxoonniha ikkiro konni lallawira worroonni qoossonna horo diafi'ranno.

3. Xaphoomu yoo mini pirezidantichi, layinki pirezidantichi, xaphoomu yoo mini yooaanchi,

**43. መብት እና ጥቅሞች የሚያሳጡ ሁኔታዎች**

1. ማንኛውም ፕሬዚዳንት፣ ምክትል ፕሬዚዳንት፣ የቢሮ ኃላፊ፣ ኮሚሽነር፣ ዋና ዳይሬክተር፣ ምክትል የቢሮ ኃላፊ፣ የሬጂኦፖሊታን ከተማ ከንቲባ፣ ምክትል ከንቲባ፣ የዞን አስተዳዳሪ፣ ምክትል አስተዳዳሪ ወይም በተመሳሳይ ደረጃ ላይ የሚገኝ የመንግሥት ተሿሚ፡-

   ሀ) በራሱ ፈቃድ ሥልጣን ከለቀቀ ወይም

   ለ) የሙስና ወንጀል ፈጽሞ በፍርድ ቤት ጥፋተኝነቱ የተረጋገጠ እንደሆነ በአዋጁ የተገለጹ መብቶችን እና ጥቅሞችን አያገኝም፡፡

2. ማንኛውም የምክር ቤቱ አፈ-ጉባኤ፣ ምክትል አፈ-ጉባኤ፣ የምክር ቤቱ ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ፣ ቋሚ ኮሚቴ ምክትል ሰብሳቢ፣ የጽህፈት ቤት ኃላፊ፣ ወይም የሬጂኦፖሊታን ከተማ አፈጉባኤ፣ ምክትል አፈ ጉባኤ ወይም በተመሳሳይ ደረጃ ላይ የሚገኙ የመንግሥት ተሿሚዎች እና የምክር ቤቱ አባላት፡-

   ሀ) በራሱ ፈቃድ ሥልጣን ከለቀቀ ወይም

   ለ) የሙስና ወንጀል ፈጽሞ በፍርድ ቤት ጥፋተኛ መሆኑ የተረጋገጠበት እንደሆነ በዚህ አዋጅ የተገለጹ መብቶችን አያገኝም፡፡

3. የጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት፣ ምክትል ፕሬዚዳንት፣ የጠቅላይ ፍርድ ቤት ዳኛ፣ የከፍተኛ

Aliidi yoo mini pirezidantichi, Aliidi yoo mini layinki pirezidantichinna qoqqowu biiro deerrinni afantano seeru allalano;-

a) Umisi fajjonni biilloonye aguriro; woy

b) Mussinnu jaddo looseenna yoote mine hunaancho ikkinota buunxoonniha ikkiro konni lallawira worroonni qoosso diafi'ranno.

**Gafa Lee**

**Addi Addi Woro**

**44. Konne Lallawa Jeefisiisate Qeecha Uynoonninsa Bissa**

Konne Lallawa jeefisiisate aante noo bissara sooreessimmate qeecha uynoonninsa:-

**1. Qoqqowu Pirezidantichi Borro Mine**

Woolootu seerubbanni uynoonni biilloonyinna loosu qeechi noo geedee hee'reenna;-

a) Biilloonyunni ka'inori qoqqowu mootimma jeefisaanno bissa sooreeyyenna biilto konni lallawinni seerroonni qoossonna horo agarantannonsa gede assanno; hasiissano

ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት፣ የከፍተኛ ፍርድ ቤት ምክትል ፕሬዚዳንት ወይም በክልሉ ቢሮ ደረጃ የሚገኝ አቃቤ ሕግ፡-

ሀ) በራሱ ፈቃድ ሥልጣኑን ከለቀቀ ወይም

ለ) የሙስና ወንጀል ፈጽሞ በፍርድ ቤት ጥፋተኛ መሆኑ የተረጋገጠ እንደሆነ በዚህ አዋጅ የተገለጹ መብቶችንና ጥቅሞችን አያገኝም፡፡

**ክፍል ስድስት**

**ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች**

**44. ይህን አዋጅ ለማስፈጸም ኃላፊነት የተሰጣቸው አካላት**

ይህንን አዋጅ ለማስፈጸም ለሚከተሉት አካላት ኃላፊነት ተሰጥቷቸዋል፡-

**1. የክልሉ ፕሬዚዳንት ጽህፈት ቤት**

በሌሎች ሕጎች የተሰጠው ሥልጣንና ተግባር እንደተጠበቀ ሆኖ፡-

ሀ) ከኃላፊነት የተነሱ የክልሉ መንግሥት አስፈጻሚ አካላት ኃላፊዎች እና ተሿሚዎች በዚህ አዋጅ የተደነገጉት መብት እና ጥቅሞች እንዲጠበቅላቸው ያደርጋል፤ የሚያስፈልጉ ማስረጃዎችን በሙሉ አጣርቶ

tajubba baalanta buuxenna qineesse hajo la’annonsa bissara soaanno.

b) Konni lallawi garinni loosoho gaamama hasiissannonsa qoqqowu mootimma sooreeyye Qoqqowu Dagitte Owaantenna Mannu Jiro Latishshi Biiro gaantanno gede assanno.

**2. Qoqqwu Amaale Mini Borro Mine**

Woolootu seerubbanni uyinoonni biilloonyinna loosu qeechi noo geedee hee’reenna;-

a) Biilloonyunni ka’inori qoqqowu seera fushshano bisi sooreeyye, dooramaanonna biilto konni lallawinni seerroonni qoossonna horo agarantannonsa gede assanno; hasiissano tajubba baalanta buuxenna qineesse hajo la’annonsa bissara soaanno.

b) Biilloonyunni ka’inori qoqqowu seera fushshano bisi sooreeyye, dooramaanonna biilto konni lallawi garinni loosoho gaamama hasiissannonsare Dagitte Owaantenna Mannu Jiro Latishshi Biiro gaantanno gede assanno.

**3. Qoqqowu Xaphoomu Yoo Mine**.

Wolu seerinni uynoonni biilloonyinna loosu qeechi noo geedee hee’reenna:-

a) Xaphoomu yoo mini pirezidanticha, layinki

እና አደራጅቶ ለሚመለከተው አካል ይልካል፤

ለ) በዚህ አዋጅ መሠረት በሥራ ላይ መመደብ ያለባቸውን የክልሉን የመንግሥት ኃላፊዎች በክልሉ የፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ቢሮ እንዲመደቡ ያደርጋል፡፡

**2. የክልሉ ምክር ቤት ጽህፈት ቤት**

በሌሎች ሕጎች የተሰጠው ሥልጣንና ተግባር እንደተጠበቀ ሆኖ፡-

ሀ) ከኃላፊነት የተነሱ የክልሉ መንግሥት ህግ አውጪ አካላት ኃላፊዎች፤ ተመራጮች እና ተሿሚዎች በዚህ አዋጅ የተደነገጉት መብት እና ጥቅሞች እንዲጠበቅላቸው ያደርጋል፤ የሚያስፈልጉ ማስረጃዎችን በሙሉ አጣርቶ እና አደራጅቶ ለሚመለከተው አካል ይልካል፤

ለ) ከኃላፊነት የተነሱ የክልሉ መንግሥት ህግ አውጪ አካላት ኃላፊዎች፤ ተመራጮች እና ተሿሚዎች በዚህ አዋጅ መሠረት በሥራ ላይ መመደብ የሚገባቸውን በክልሉ የፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ቢሮ እንዲመደቡ ያደርጋል፡፡

**3. የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት**

በሌሎች ሕጎች የተሰጠው ሥልጣንና ተግባር እንደተጠበቀ ሆኖ፡-

ሀ) የጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት፣

pirezidanticha, xaphoomu yoo mini yooaano, aliidi yoo mini perezidanticha, layinki pirezidanticha konni lallawira seerroonni qoossonna horo agarantannonsa gede assanno; hasiissano tajubba baalanta buuxenna qineesse hajo la’annonsa bissara soaanno.

b) Biilloonyunni ka’inore xaphoomu yoo mini pirezidanticha, layinki prezidanticha, aliidi yoo mini pirezidanticha, layinki pirezidanticha konni lallawi garinni yooaanchimmate loosira gaamama hasidhuro gaamantanno gede assanno.

c) Kunni quwira cinaachu quwa 3 fadalete aante (b) aana seerronnihu hee’rirono yoaanchimmate loosira gaamama dandaannohu kunni lallawi aana worroonni qoossonna horo baantoonnisikkiha ikkiro callaati.

**4. Qoqqowu Farcote Biiro**

Wolootu seerubbanni uynoonni biillonyinna loosu qeechi noo gedee hee’reenna:-

a) Qoqqowu farcote biiro seeru allaalaanora kunni lallawinni seerroonni qoossonna horo agarantannonsa gede assitanno; hasiissano tajubba baalanta buuxxenna qineessite hajo la’annonsa bissara sokkanno.

b) Biilloonyunni ka’inore farcote biiro seeru allaalaano konni lallawi garinni wolu loosira gaamama hasidhannore gaamantanno gede assitanno.

c) Kunni quwira cinaachu quwa 4 fadalete

ምክትል ፕሬዚዳንት፣ የጠቅላይ ፍርድ ቤት ዳኞች፣ የከፍተኛ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት፣ ምክትል ፕሬዚዳንት በዚህ አዋጅ የተደነገጉት መብት እና ጥቅሞች እንዲጠበቅላቸው ያደርጋል፤ የሚያስፈልጉ ማስረጃዎችን በሙሉ አጣርቶ እና አደራጅቶ ለሚመለከተው አካል ይልካል፤

ለ) ከኃላፊነት የተነሳ የጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት፣ ምክትል ፕሬዚዳንት፣ የከፍተኛ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት ወይም ምክትል ፕሬዚዳንት በዚህ አዋጅ መሠረት በዳኝነት ሥራ ላይ መመደብ የሚፈልጉትን እንዲመደቡ ያደርጋል፤

ሐ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 በፊደል ተራ (ለ) የተደነገገው ቢኖርም በዳኝነት ሥራ መመደብ የሚችለው በዚህ አዋጅ የተደነገጉትን መብትና ጥቅሞች ያልተከፈለው እንደሆነ ብቻ ነው።

**4. የክልሉ ፍትህ ቢሮ**

በሌሎች ሕጎች የተሰጠው ሥልጣንና ተግባር እንደተጠበቀ ሆኖ፡-

ሀ) የክልሉ ፍትሕ ቢሮ አቃቢያነ ሕግ በዚህ አዋጅ የተደነገጉት መብቶች እና ጥቅሞች እንዲጠበቅላቸው ያደርጋል፤ የሚያስፈልጉ ማስረጃዎችን በሙሉ አጣርቶ እና አደራጅቶ ለሚመለከተው አካል ይልካል፤

ለ) ከኃላፊነት የተነሱ የፍትሕ ቢሮ አቃቢያነ ህግ በዚህ አዋጅ መሠረት በሌላ ሥራ መደብ ላይ መመደብ የሚፈልጉ ከሆነ እንዲመደቡ ያደርጋል፤

aante (b) aana seerronnihu hee’rirono seeru allaallaanchimma loosira gaamama dandaannohu kunni lallawi aana worroonni qoossonna horo baantoonnisikkiha ikkiro callaati.

5. **Qoqqowu Dagitte Owaantenna Mannu Jiro Latishshi Biiro**

Wolootu seerubbanni uynoonni biilloonyinna loosu qeechi noo gedee hee’reenna:-

a) Biilloonyunni ka’inore jeefisiisaano bissa sooreeyye, farcote biiro seeru allaalaano, qoqqowu Amaale Mini miilla, yooaanonna seeru allaalaano qoossonna horo lainohunni shiqqanno tajubba halaalaanchimma buuxatenni gimmite fultanno gede assitu gedensaanni hasiisanno baatooshshe jeefissano gede Faynaansete Biirora sayissanno;

b) Mittu mittunku aleenni tittiroonni bissa qoossonna horo qoossaanonna maatensa tittirshunni maareekkite amaddanno;

c) Babbaxitino yannara kalaqantara dandiitanno dikkote waagi soorro kaima assatenni babbaxitino horo aana xiinxallo assite loosu aana hossanno gede assitanno; jeefishshano harunsitanno;

d) Biilloonyunni ka’ino soorreeyyera uynanni babbaxxitino owaante rakkinota, taalashshonna deerrase agartinota ikkase harunsitanno; buuxxanno;

e) Konni lallawi ledo amadame qoossotenna horote hajubba lainohunni shiqqano koffeenyubba haadhanno, buuxxanno, taashshote qaafo adhitanno, qaafo adhinanni gedeno assitanno;

ሐ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 4 በፊደል ተራ (ለ) የተደነገገው ቢኖርም በአቃቤ ሕግነት ሥራ መመደብ የሚችለው በዚህ አዋጅ የተደነገጉትን መብትና ጥቅሞች ያልተከፈለው እንደሆነ ብቻ ነው፡፡

5. **የክልሉ ፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ቢሮ**

በሌሎች ሕጎች የተሰጠው ሥልጣንና ተግባር እንደተጠበቀ ሆኖ፡-

ሀ) ከኃላፊነት የተነሱ የሥራ አስፈጻሚ አካላት ኃላፊዎችና የፍትሕ ቢሮ አቃቢያን ሕግ፤ የክልሉ ምክር ቤት አባላት፣ ዳኞች እና አቃቢያን ሕግ መብት እና ጥቅሞች አስመልክቶ የቀረበውን ማስረጃ ትክክለኛነት በማረጋገጥ ግምቱን እንዲወጣ ካደረገ በኋላ አስፈላጊው ክፍያ እንዲፈጸም ለፋይናንስ ቢሮ ያስተላልፋል፤

ለ) እያንዳንዳቸው ከላይ የተዘረዘሩ አካላት የመብት እና ጥቅሞች ባለመብቶችን እና የቤተሰባቸውን ዝርዝር በመመዝገብ ይይዛል፤

ሐ) በተለያየ ጊዜ ሊፈጠር የሚችለውን የዋጋ ተመን ለውጥ መሠረት በማድረግ በተለያዩ ጥቅሞች ላይ ጥናት በማካሄድ ሥራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፤ አፈጻጸሙን ይከታተላል፤

መ) ከኃላፊነት ለተነሱ ኃላፊዎች የሚሰጡ የተለያዩ አገልግሎቶች የተፋጠነ፣ ፍትሃዊ እና ደረጃቸውን የጠበቁ መሆናቸውን በቅርበት ይከታተላል፤ ያረጋግጣል፤

ሠ) ከዚህ አዋጅ ጋር ተያይዞ የመብት እና ጥቅሞች ጉዳዮችን አስመልክቶ የሚቀርቡ ቅሬታዎችን ይቀበላል፤ ያጣራል፤ የማስተካከያ እርምጃ ይወስዳል፤ እንዲወሰድ ያደርጋል፤

**6. Qoqqowu Faynaansete Biiro**

Wole seerubbanni uynoonni biilloonyinna loosu qeechi noo gedee hee'reenna:-

a) Konni lallawinni gumulloonni qoossonna horo jeefisate ikkitannota bajeette mootimma gaantano gede assitanno;

b) Dagitte Owaanttenna Mannu Jiro Latishshi Biironni shiqqanno qoossonna horo tajubba aana kaima assite hasiishshu garinni baatooshshe jeefissanno.

**45. Wodhonna Biddissa Fushshate Biilloonye**

Qoqqowu Jeefisiisaanote Amaale Mini konne Lallawa jeefisiisate wodhonna biddissa fushshara dandaanno.

**46. Jeefishshu Noonsakki Seerubba**

1. Qoqqowu Lallawi kiiro 8/2012 M.D garinni loosu aana hosanno gede fajjinoonnihu Wodiidi Qoqqowihu Biillonyunni Ka'ino Aliidi Loosu Sooreeyye, Amaalete Mini Miillanna Yooaanote Qoossonna Horo Murate fulino Lallawi kiiro 148/2004 konni Lallawinni riqiwamino.

**6. የክልሉ ፋይናንስ ቢሮ**

በሌሎች ሕጎች የተሰጠው ሥልጣንና ተግባር እንደተጠበቀ ሆኖ፡-

ሀ) በዚህ አዋጅ የተደነገጉትን መብት እና ጥቅሞች ለማስፈጸም የሚውል በጀት በመንግሥት እንዲመደብ ያደርጋል፤

ለ) ከፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ቢሮ በሚቀርብለት የመብት እና ጥቅሞች ማስረጃዎች ላይ በመመስረት አስፈላጊ ክፍያዎችን ይፈጽማል፤

**45. ደንብና መመሪያ የማውጣት ሥልጣን**

የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ይህን አዋጅ ለማስፈጸም ደንብ እና መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

**46. ተፈጻሚነት የሌላቸው ሕጎች**

1. በክልሉ አዋጅ ቁጥር 8/2012 ዓ.ም መሠረት ሥራ ላይ እንድውል የተፈቀደዉ የደቡብ ብሔር፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል ከኃላፊነት የተነሱ ከፍተኛ የሥራ ኃላፊዎች፣ የምክር ቤት አባላትና ዳኞች መብቶችና ጥቅሞች ለመወሰን የወጣዉ አዋጅ ቁጥር 148/2004 በዚህ አዋጅ ተተክቷል፡፡

2. Kunni lallawi ledo kibbamannohu hiikku seerino woy rosichu loossa konni lallawi giddo hanqafantino hajubba aana jeefishshu dihee’rannonsa.

**47. Lallawu Kaajjanno Yanna**.

Kuni Lallawi barra Ammajje 20/2017 M.D kaajjinshihunni hanafe loosu aana hosannoha ikkanno.

**Desta Ledamo**

**Sidaamu Dagoomu Qoqqowi Mootimma Pirezidanticha**

2. ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረን ማንኛውም ህግ ወይም ልማዳዊ አሠራር በዚህ አዋጅ ውስጥ በተካተቱ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖራቸውም፡፡

**47. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ አዋጅ ከጸደቀበት ከዛሬ የካቲት ፳ ቀን ፳፻፲፯ ዓ.ም ጀምሮ ሥራ ላይ ይዉላል፡፡

**ደስታ ሌዳሞ**

**የሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ርዕሰ መስተዳድር**